እናድ
# አዲስ ዘመን
ዓርብ
81ኛ ዓመት ቁጥር 357 ነሐሴ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

# መንግስትን ከአሸባሪ ድርጅት ጋር የሚያመሳስሉ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተጠየቀ

## - ዲፕሎማቶች የኢትዮጵያን የሠላም ጥረት አድንቀዋል

**አዲሱ ገረመው**



ፎቶ፡ በፀሐይ ንጉሤ

**አቶ ደመቀ መኮንን**

አዲስ አበባ፡- መንግስትን ከህገ ወጥ አሸባሪ ድርጅት ጋር የሚያመሳስሉ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን አሳሰቡ። የኢትዮጵያ መንግስት የሠላም ጥረት በዲፕሎማሲው ማህበረሰብ ዘንድ አድናቆት ማግኘቱም ተጠቆመ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን መቀመጫቸውን በአዲስ አበባ ላደረጉ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮች፣ የሚሲዮን መሪዎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች በኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ትናንት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ጉዳይ ሚዛናዊና ገለልተኛ አቋም ሊያንጸባርቅ ይገባል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ግጭቱን የሚያባብሱና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥሉ እርምጃዎችንም እንዲያቆሙ አሳስበዋል። የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለሠላም አማራጩ አፍሪካ ህብረትን የመደገፍ እድል እንዳለውም ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ፤ አገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ኢትዮጵያ ግጭት ውስጥ እንዳትገባ እያደረጉ ያለውን የሰላም እገዛ አድንቀዋል። በአንጻሩ አንዳንዶች ግጭቱን በመደገፍ በሚዲያ ጭምር አሸባሪውን ቡድን እያገዙ እንዳሉ ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት ግጭቶች እየተባባሱ ቢሄዱም የኢትዮጵያ መንግስት ሰላምን ለማስፈን ቁርጠኛ ነው፤ በአንጻሩ የሕወሓት ቡድን በአፍሪካ ህብረት የሚመራውን የሰላም ሂደት በማጣጣል ላይ ይገኛል።

መንግስትን መውቀስ እና ማጥላላት፤ የይስሙላ ድሎችን ማረጋገጥን ጨምሮ የሕወሓት ሀሰተኛ ፕሮፖጋንዳ ቢኖርም፤ የኢትዮጵያ መንግስት የመላው ኢትዮጵያውያንን ደህንነት የመጠበቅ ህገ መንግስታዊ ግዴታውን እንደሚወጣም አስረድተዋል።

ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው እንዳነሱት፤ የኢትዮጵያ መንግስት የተኩስ አቁም ስምምነቱን በማክበር ለሠላም አማራጮች ሲተጋ አሸባሪው ሕወሓት በበኩሉ ለሌላ ዙር

መንግሥትን ከአሸባሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# ሕወሓት ወረራውን እያስፋፋ መጬኹን ቀጥሉበታል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ወረራውን እያስፋፋ መጬኹን እንደቀጠለ መሆኑን የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ገለፀ፡፡

የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው አሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን ገፍቶ በየአቅጣጫው ከለኮሰው እሳት ሰይታቀብ ወረራውን እያስፋፋ መጬኹን መቀጠሉን አስታውቋል፡፡

ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን ገፍቶ በየአቅጣጫው በለኮሰው እና ዛሬም እያስፋፋ ባለው እሳት ንጹሐን እየተገደሉ ከመሆኑም ባሻገር ሕዝብ እየተፈናቀለ፣ ንብረትም እየወደመ መሆኑን መግለጫው አብራርቷል።

አሁን እንደሚታየው አሸባሪውን ሕወሐት ከሀገር አጥፊነት ተግባሩ የማስቆም ግዴታ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ላይ መውደቁን በማተት፤ ቡድኑን ከሀገር አጥፊነት ተግባሩ ለማስቆም ሕዝብና መንግሥት የሚገደዱባቸውን ምክንያቶች አስቀምጧል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት፣ የሽብር ቡድኑ ሰላምን እንዳያደፈርስና ሀገርን እንዳያፈርስ መከላከል እንደሚገባ በመጠቆም፤ ሕወሓት ወደ ትግራይ የሚላከውን ዕርዳታ ለተቸገረው ሕዝብ እንዳይደርስ እያደረገ መሆኑንም አንስቷል፡፡

ቡድኑ ለተቸገረው ሕዝብ የሚላከው ዕርዳታ በተቃራኒው ለጦርነት እንዲውል እያደረገ በመሆኑ መንግሥት ርዳታው ለተረጂው ሕዝብ እንዲደርስና ትግራይ ውስጥ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሕዝቡን ከችግር የመከላከል ግዴታ ስላለበት ሕወሓትን ከአገር አጥፊነት ተግባሩ ለማስቆም እንደሚገደድ አብራርቷል፡፡

ሕወሓት በእኩይ ተግባሩ ሕዝብን በረሃብ ለመቅጣት አቅዶ ተደጋጋሚ ጦርነት የሚከፍተው በክረምት የግብርና ወቅት በመሆኑ መንግሥት ወረራውን እየተከላከለ

ሕወሓት ወረራውን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ በሀዳሽ አብርሃ

ገጽ 4

## የትግራይ የሃይማኖት አባቶች የክልሉን መሪዎች በመገሰጽ ወደሰላማዊ ውይይቱ እንዲመለሱ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ክላሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

## ምዕራባዊያን

ሕወሓት ሕፃናትን በጦርነት ሲያሳትፍ የማያወግዙት ጉዳዩ ከዋናው አጀንዳቸው ጋር ስለሚጻረር ነው

ገጽ 3



# “ሀገራችንንና ሕዝባችንን በሕወሓት ከተጋረጠበት አደጋ ለመከላከል መንግሥት የሚወስደውን ሕጋዊ እርምጃ እንደግፋለን”

## - በሰሜን አሜሪካ የሲቪክ ማህበራት ህብረት ጥምረት

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት “ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመነጋገር ሰላም የማስፈን” ፅኑ አቋሙ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችንን እና ሕዝባችንን በሕወሓት ከተጋረጠበት የጦርነት አደጋ ለመከላከል የሚያደርገውን ማንኛውንም ህጋዊ እርምጃ እንደሚደግፍ ከሰሜን አሜሪካ የሲቪክ ማህበራት ህብረት ጥምረት ገለጸ።

የሰሜን አሜሪካ የሲቪክ ማህበራት ህብረት ጥምረት ለዝግጅት ክፍላችን በላከው መግለጫ እንዳለው፤ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን የለውጥ ጎዳናውን በማደናቀፍ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከመረገጥ እና ከመዘረፍ የሚገታውን፣ ለሀገር ክብር አንድነት ቦታ የሚሰጠውን ለውጥ የማይቀበል መሆኑን በተግባር ሲያሳይ ቆይቷል። የኢትዮጵያ መንግሥት “ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመነጋገር ሰላም የማስፈን” ፅኑ አቋሙ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችንን እና ሕዝባችንን በሕወሓት ከተጋረጠበት የጦርነት አደጋ ለመከላከል የሚያደርገውን ማንኛውንም ህጋዊ እርምጃ እንደሚደግፍ አስታውቋል።

ቡድኑ የሕዝብ ጠባቂ የሆነውን የሀገር መከላከያ ሰራዊት የሰሜን ዕዝ በማጥቃት ሀገሪቱን ለውጭ እና ለውስጥ አደጋ አጋልጧል ያለው ሕብረቱ፤ በአማራና በአፋር ክልሎችና ህዝብ ላይም የዕብሪት ወረራ በመፈጸም ከባድ የዘር ጭፍጨፋ በበርካታ የአማራና የአፋር አካባቢዎች አድርሷል። የትግራይን ክልል የጦር አውድማ በማድረግም ሕዝቡን ታሪክ ይቅር የማይለውን ክህደትና በደል ፈጽሞበታል ብሏል።

የኢትዮጵያ መንግስት “ጦርነት ይብቃን፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተነጋግረን ችግራችንን እንፍታ” በሚል እምነት ለሰላም ቅድሚያ መስጠቱን አድንቆ፤ ሕወሓት ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት ጀምሯል። የዓለም አቀፍን የሰብአዊ መብትና የጦርነት ድንጋጌን ህግ በመጣስ ህፃናትን ለጦርነት ማሰለፉንም አውስቷል።

ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል መርህ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሰየመውን የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሌሴጎን ኦቦሳንጆ አልቀበልም በማለት አጠቃላይ የሰላም ሂደቱን ማደናቀፍ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ህብረት ያለውን ንቀት አሳይቷል ያለው የሕብረቱ መግለጫ፤ የኤርትራን መንግሥትና ሕዝብ ለመውጋት እየዛተ ሲሆን፤ የትግራይን ሕዝብ ወንድሙ ከሆነው የአማራና የአፋር ሕዝብ ጋር ደም ለማቃባት የቻለውን ሁሉ እያደረገ እንደሚገኝም አመላክቷል።

በተጨማሪም ሕወሓት ለሶስተኛ ዙር ጦርነት መጀመር “የአሜሪካ ዴሞክራት ፓርቲ መራሹ መንግስት በውጪ ፖሊሲ ድክመቱ ምክንያት አለም አቀፍ ግጭቶች ተበራክቷል” የሚል የሪፐብሊካንን ጫና ለማስተንፈስ ደሃ ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ የመጣልም ሆነ ሌላ ጫና የማድረግ ውስጣዊ የፖለቲካ ግፊት እንዲኖር በመፈለግ ጭምር ነው የሚል እምነት እንዳለውም አስገንዝቧል።

የኢትዮጵያ መንግስት “ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመነጋገር ሰላም የማስፈን” ፅኑ አቋሙ እንደተጠበቀ ሆኖ አገራችንን እና ህዝባችንን በሕዋሓት ከተጋረጠበት የጦርነት አደጋ በኃይል ለመከላከል የሚያደርገውን ማንኛውንም ህጋዊ እርምጃ እንደግፋለን፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፣ የአማራ ልዩ ኃይል፣ ፋኖና የአፋር ልዩ ኃይል የሕዋሓትን እኩይ ጦርነት ለመመከት በየግንባሩ እየከፈለ ያለውን መስዋእትነት በማድነቅ፣ በውጭ የሚኖር የዳያስፖራ አካላት ሙሉ ድጋፍ እንደሚሰጥ




አመልክቶ፤ ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል መርህ የሰላም ድርድሩን እንዲመሩ በአፍሪካ ህብረት የተሰየሙት ፕሬዚዳንት ኦሌሴጎን ኦቦሳንጆን እያደርጉ ላሉት ጥረትም ሙሉ ድጋፍ እንሰጣለን፤ በአንጻሩም አደራዳሪ ለመቀየር የሚደረግን ማንኛውንም ጫና በጥብቅ እንቃወማለን ብሏል።

# የዜጎችን የኑሮ ሸክም እያቃለለ ያለው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

በኃይሉ አበራ

ኑሮ ቢጫናቸውም እጅ አልሰጡም። ዛሬም የአቅማቸውን ያህል ይታትራሉ። ያም ሆኖ ግን አሮጌው የቀበሌ መኖሪያ ቤታቸው ከዛሬ ነገ ላያቸው ላይ እንዳይወድቅ በመስጋት ፈጣሪንም መለመናቸውን አላቆሙም። ምክንያቱም ቤታቸው ከማርጀቱ የተነሳ በአብዛኛው በክረምቱ ጣራው ከማፍሰሱም በላይ በአንድ ጎን ተንጋዶ ከዛሬ ነገ እወድቃለሁ እያለ እያስፈራራ ነውና።

ስፍራው አራዳ ክፍለከተማ ነው። በተለምዶ 15 ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ወይዘሮ ጥሩነሽ ሞገስ በዚህ ቤት ውስጥ እድሜ ዘመናቸውን ኖረዋል። አሁን ግን አቅማቸው ስለደከመና ቤቱም እያረጀ በመሄዱ ሸክሙ ከብዷቸዋል።

ይህንን የተረዳው የወረዳው አስተዳደር ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በመሆን ሰሞኑን ቤታቸውን አድሶላቸዋል። በዚህም ወይዘሮ ጥሩነሽ ደስታቸው ወደር የለውም።

“በደሳሳ ቤቱ ከአንድ አልጋ በስተቀር መተላለፊያ እንኳን የሌለው በመሆኑ በጭንቅ እና በችግር እየኖርኩበት ነው። ቀኑ ደርሶ ፈጣሪ ቀጥሮልኝ አሁን ቤት ሊታደስልሽ ነው ሲሉኝ ለማመን ሁሉ ከብዶኛል” ይላሉ ወይዘሮ ጥሩነሽ።

ያረጀው ቤት እንዳይፈርስባቸው እና ቅያሬ እንዲሰጣቸው ቀበሌ በተደጋጋሚ እያመለከቱ እንደነበር የሚናገሩት ወይዘሮ ጥሩነሽ፤ “እኔ ታምሜአለሁ፣ መስራት አልችልም፣ ጉሊት እየዋልኩ ነው የምመጣው ብዬ ሳመለክት ፍቃድ ከመስጠት በቀር ማደስ አንችልም የሚል ምላሽ ተሰጥቶኝ ተስፋ ቆርጬ ነበር ብለዋል።

የደም ግፊት ታማሚ መሆናቸውን የገለጹት ወይዘሮ ጥሩነሽ ጉሊት ውዬ ማታ ስገባ ይናድብኝ ይሆናል በሚል በስጋት ሲኖሩ መቆየታቸውን ጠቁመዋል።

“ከፍ አላልኩም እንጂ ከጃንሆይ ዘመን ጀምሮ እዚችው ሰፈር እየኖርኩ ነው፤ በጃንሆይ ዘመን ስኖርበት የነበረውን አንድ ቤት ደርግ ወስዶ በምትኩ አሁን ያለሁበትን ቤት ለጊዜው በሚል ለአንድ ወር ሰጥተውኝ ነበር። አሁን 40 ዓመት ሙሉ እዚሁ እየኖርኩ ነው ብለዋል። ሲያመኝ እተኛለሁ ሲሻለኝ ጉሊት እየሸጥኩ ኑሬዬን እገፋለሁ ሌላ ገቢ የለኝም” አሁን ግን መንግስት በዚህ ደረጃ ስላየኝ በጣም ደስተኛ ነኝ ሲሉ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ጥሩነሽ ጉልትም ተቀምጠን፣ ሸጠንም ሆነ ለምነን የምንኖረው አገር ሰላም ሲሆን በመሆኑ ፈጣሪ አገራችንን ሰላም ያድረግልን ሲሉም ተናግረዋል።


ወይዘሮ ጥሩነሽ ሞገስ

ከኢትዮጵያዊ የመረዳዳት እሴቶቻችን የሆነው ማዕድ ማጋራት፣ አቅመ ደካሞችን የመደገፍ ባህላችን ተጠናክሮ ቀጥሏል። በዘንድሮ የክረምት በጎ ተግባር በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ አቅመ ደካሞች የቤት እድሳት፣ የማዕድ ማጋራት እና ሌሎች በጎ ተግባራት ተጠናክረው ቀጥለዋል። በሰኔ ወር ብቻ በከተማ አስተዳደሩ ከ60 ሺህ በላይ ማዕድ የማጋራት ስራ አከናውኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህጻናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ለሚገኙ ከ200 በላይ አቅመ ደካማ እናቶች ማዕድ አጋራ። ለአንድ አቅመ ደካማ እናትም በአንድ ወር ውስጥ የሚጠናቀቅ የቤት እድሳት አስጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሀና የሺንጉስ የዚህ ድጋፍ መነሻ እርስ በእርሳችን መረዳዳት እና መደጋገፍ ስለሚገባ ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰው ከራሱ በላይ ለጎረቤቱ ማሰብ አለበት ባሉት መሰረት ያለንን በማካፈል ማንም የሚራብባት አገር ሳትሆን ሁላችንም ጠግበን የምናሳልፍባት እንድትሆን ካለን ላይ ለማቋደስ ነው ድጋፉን ያደረግነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሴቶች ህጻናት እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሰፊ የሆነውን የማህበረሰብ ክፍል ማለትም ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ አረጋዊያንን ፣ አካል ጉዳተኞችን እና ጎዳና ተዳዳሪዎችን ያቀፈ መሆኑን የገለጹት ኃላፊዋ፤ ለእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚደረጉ ድጋፎችን በመንግስት በጀት ብቻ ማሳካት የማይቻል በመሆኑ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር መስራት ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያዊነታችን ባህል አብሮ መብላት በመሆኑ የእናታችን ቤት ባዶ ውሎ እያደረ ባዶ ሆዳቸውን እያሳለፉ እኛ ጠግበን ማደር አንችልም ብለዋል።

በመሆኑም ከ200 በላይ ለሚሆኑ አቅመ ደካሞች የተደረገው የማዕድ ማጋራት ቢሮው መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመሆን ያሰባሰባቸው እንደሆኑ ጠቁመዋል።

የወረዳ ሰባት ሴቶች እና ሕጻናት ልማት አስተዳደር ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ አበበ በበኩላቸው፤ በወረዳው ከ200 በላይ ለሚሆኑ አቅመ ደካማ እናቶች በአይነት የተደረገው ድጋፍ እና ደጋፊ ጧሪ አጋዥ የሌላትን አንዲት እናት ቤት የእድሳት ግንባታ ስራ የተጀመረበት በመሆኑ ቀጣይ አበረታች ስራዎች ስለመሰራታቸው ማሳያዎች ናቸው ብለዋል።

ድጋፉ በመተሳሰብ፣ አብሮ በመተጋገዝና በመረዳዳት ያካበትነው የቆየ እሴታችን መበረታታትና ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ከዚህ በፊትም በወረዳው መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና ባለሀብቶች በዓላትን በማስመልከት እና ከክረምቱ ጋር ተያይዞ የድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርቡም አስተዳደሩ በደረጃ በሚያቀርበው መረጃ መሰረት እየተደገፉ የመጡ አሉ ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ሴቶች ህጻናት እና ማህበራዊ ቢሮ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመሆን በአንድ ወር ጊዜ ለማከናወን በተጀመረው የአንዲት አቅመ ደካማ ቤት የማደስ ስራ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይኖሩ በማድረግ በተቀመጠ ጊዜ እንዲጠናቀቅ እንሰራለን ብለዋል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዘንድሮው ክረምት በአዲስ አበባ በተከናወነው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከሶስት ቢሊየን ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ ተደርጓል።

# አሸባሪው ሕወሓት ዛሬም ለሰላማዊ ዜጎች ሞት፣ መፈናቀልና ስደት ምክንያት ሆኗል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ከውጪ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በማበር እና በመንግስት በኩል የተደረገውን የተናጠል ተኩስ አቁም ስምምነት ወደ ጎን በመጣል እንዲሁም ለሰላም የተደረጉ ጥሪቶችን ባለመቀበል ኢትዮጵያን ለመበታተን ለሦስተኛ ጊዜ በከፈተው ጦርነት አሁንም ለሰላማዊ ዜጎች ሞት፣ መፈናቀልና ስደት ምክንያት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ በትናንትናው ዕለት በተደረገው የተቋሙ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያን ሰላም የማይፈልገው አሸባሪው ሕወሓት መንግስት ሳይወድ በግድ ሌላ ጦርነት እንዲገባ አድርጎታል። መንግስት አሁንም ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት ቡድኑ የወረረውን አካባቢ በመልቀቅ ወደ ሰላም እንዲመለስ እያደረገ ይገኛል። ችግሮችን በውይይት ብቻ እንዲፈቱ አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ ጥረቱ ቀጥሏል።


የሲቪል ማህበረሰቦች ድርጅቶች ባለሥልጣን ዓመታዊ ስብሰባ

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የቡድኑን አካሄድ እንዲገንዘብ፣ እንዲያወግዝና ሰላም ብቸኛው አማራጭ ሆኖ እንዲቀርብ ተገቢውን የማሳወቅ ስራ መፈጸም እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያውያን አገራዊ አንድነታችንን በማጠናከር ፊታችንን ወደ ልማት ልናዞር ይገባናል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በጦርነት ውስጥ ሆኖ ዘላቂ ልማት ማሰብ እንደማይቻል ገልፀው፤ በድህነት ውስጥ ያለችን አገር በጦርነት ማዕበል ውስጥ መቆየት አይገባትም ሲሉ አሳስበዋል።

ኢትዮጵያን ያጋጠሟት ፈታናዎች ሊበታትኗት ባይቻላቸውም ጠባሳዎች እንደጣሉባት ያወሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህንን የታሪክ ገጽታ ማረም ይገባናል። ለቀጣዩ ትውልድ ሰላምን፤ ልማትንና ህብረብሔራዊ አንድነትን ማውረስ ለመቻል ሁሉም ዜጋና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሕወሓትን አካሄድ እንዲገነዘብ፣ እንዲያወግዝና ሰላም ብቸኛው አማራጭ ሆኖ እንዲቀርብ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተገቢውን የማሳወቅ ስራ መፈጸም እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

አቶ ጂማ እንደተናገሩት፣ በተጀመረው አገራዊ ለውጥ የተረጋጋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መሠረቶችን ለመጣል እንዲቻል፤ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ሰላም መስፍንና ብልጽግና መረጋገጥ ድርጅቶቹ ከፍተኛ ደርሻ አላቸው። ይህን እውን በማድረግ ከድህነትና ከኋላቀርነት ኢትዮጵያን ለማላቀቅ ዘርፈብዙ ሥራዎች ተጀምረዋል። የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች ይህ እንዲሳካ ሊረባረቡ ይገባል።

ኢትዮጵያ በብዙ ፈተናዎች መካከል ያለች አገር ናት ያሉት አቶ ጂማ፤ የዴሞክራሲ ባህል ያለመጎልበት፣ ጂኦፖለቲካዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ ድህነትና የሰላም እጦት ከአሸባሪው የሕወሓት ቡድን የተከፈቱትን ተደጋጋሚ ጦርነቶች ተጨምሮ ለአገራዊ አንድነታችን ትልቁ ፈተና ሆኖብናል ሲሉ ገልፀዋል።

ድርጅቶቹ ከባህሪያቸው የተነሳ ፈተናዎች ወደ መልካም አገራዊ ዕድል የመቀየር አቅም እንዳላቸው በመጠቆም፤ በተለይም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እውነታውን እንዲገነዘብ በማድረግ በኢትዮጵያ የሚደረግ ያልተገባ ጫናን ለመቋቋም ይቻል ዘንድ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ጠይቀዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘውም፣ በጦርነቱ ምክንያት ለመፈናቀል የተዳረጉ ወገኖችን የማገዝ ሥራ አሁንም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

---


አቶ ኤፍሬም ማዴቦ

## ምዕራባውያን ሕወሓት ሕፃናትን በጦርነት ሲያሳትፍ የማያወግዙት ጉዳዩ ከዋናው አጀንዳቸው ጋር ስለሚጻረር ነው

**በጸጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ፡- ምዕራባውያን ሕወሓት ዕድሜያቸው ለጦርነት ያልደረሱ ህጻናትን በጦርነት ሲያሳተፉ አለማውገዛቸው፤ ጉዳዩ ከዋናው አጀንዳቸው ጋር ስለሚጻረር ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኝ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ገለፁ።

አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የምዕራባውያን ድርጅቶች በተለይ ዩኒሴፍ ዕድሜያቸው ለጦርነት ያልደረሱ ብዙ ህጻናት በፎቶግራፍና ቪዲዮ በተደገፈ መልኩ መስመሩን ሞልተው ወደ ጦርነት ቦታ ሲሄዱና ሲሳተፉ ቢያዩም ማሳየት፣ መናገርና መኮነን አልፈለጉም። ምዕራባውያን መንግስታትና የራሳቸው ሚዲያዎች የዘመቱት ኢትዮጵያ ላይ እንጂ ወንጀለኛ ላይ አይደለም ብለዋል።

ዓላማቸውም ምን እንጠቀማለን እንጂ ኢትዮጵያ ከዚህ ጦርነት እንዴት ትወጣለች የሚል አይደለም ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ የእነሱ አላማ ብሔራዊ ጥቅማቸውን ከሚያስጠብቅላቸው አካል ጋር ወግነው መቆም ነው፤ አለማውገዛቸው ጉዳዩ ከራሳቸው ከትልቁ ወይም ከዋናው አጀንዳቸው ጋር ስለሚጻረር ነው ብለዋል።

ምዕራባውያን ሰብአዊ መብት ተጣሳ የሚሉት አገር ከእነሱ ጋር የፖለቲካ ግጭት ወይም የእነሱን ዋነኛ የፖለቲካ አላማ የማያራምድ ሲሆን ብቻ ነው ብለዋል።

በፊት በአንድ አገር ዕድሜው ያልደረሰ ህፃን በጦርነቱ ላይ ሲሳተፍ ካገኙ ውግዘቱና መኮነኑ ተያይዞ ይመጣ ነበር ያሉት አቶ ኤፍሬም፤ ሕወሓት ከ1983 ጀምሮ የሰራቸውን በደሎች በአመታዊ መግለጫቸው ቢያወጡም ቡድኑን ኮንነው እንደማያውቁት አስረድተዋል።

ለእነሱ ቀዳሚው ተግባራቸው ብሔራዊ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ሲሆን አጀንዳቸው ሰብአዊ መብት ነው። በሌሎች አገሮች እንኳን ሕጻናት በጦርነት መሳተፍ ይቅርና በርካሽ የሰው ጉልበትና ዕድሜያቸው ለስራ ያልደረሱ ህጻናት ያመረቷቸውን ምርቶች አንገዛም የሚል ንቅናቄ እንዳለ የጠቆሙት አቶ ኤፍሬም፤ በኢትዮጵያ ላይ እየሆነ ያለው ነገር የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቅ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

አሁን ያለው መንግስት እንደባለፉት 27 አመታት ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ መንግስት እንዲሆን ይፈልጋሉ። ለዚህ ተስፋችን ነው ብለው የሚያምኑት ደግሞ ሕወሓትን ነው ብለዋል።

ሕወሓት የእነሱን ጥቅም እስካስጠበቀ ድረስ የሰው ማዕበል ተጠቅሞ እልቂት ቢፈፅምም ግድ አይሰጣቸውም። ሕወሓት እድሜያቸው ለጦርነት ያልደረሱትን ህጻናትን ማሰለፍም ሆነ የሰው ማዕበል መጠቀም ለእነሱ ጉዳያቸው አይደለም። መንግስት ያን ፈፅሞ ቢሆን ኖሮ ግን አለምን ያነቃንቁ ነበር ሲሉም ተናግረዋል።

---

# ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም በዲጂታል የታገዘ አሰራርን መዘርጋት ያስፈልጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግና ውስን የሆነውን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም በዲጂታል የታገዘ አሰራርን መዘርጋት እንደሚያስፈልግ የኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ።

ኢትዮ ቴሌኮምና የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ክፍያን በቴሌ ብር መፈፀም የሚያስችል ስምምነት በተፈራረሙበት ወቅት የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ እንደገለጹት፤ ኩባንያው ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በትኩረት እየሰራ ነው። ጊዜን ጨምሮ ያለንን ውስን ሀብት በአግባቡ ተጠቅመን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ለማግኘት ሁሉም ተቋማት በዲጂታል የታገዘ አሰራርን መከተል አለባቸው።



ኢትዮ ቴሌኮምና የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ስምምነት ተፈራርመዋል

ተቋማት ዘመናዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ኢትዮ ቴሌኮም ምቹ አሰራሮችን እየዘረጋ ነው ያሉት ስራ አስፈጻሚዋ፤ የዲጂታል ኢትዮጵያን ሃሳብ እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል። ኢትዮ ቴሌኮም በጥሬ ብር ይደረግ የነበረውን እንቅስቃሴ በቴሌብር ማድረጉ ጊዜና ወጪን ከመቆጠቡ ባሻገር ለተቋማት ጥቅሙ የጎላ ነው። እንዲሁም ደንበኞች ሳይንገላቱና ብዙ ጊዜን ሳያባክኑ እርካታ ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ እያደረገ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም 23 ነጥብ 2 ሚሊዮን የቴሌ ብር ደንበኞች እንዳሉት የገለጹት ስራ አስፈጻሚዋ፤ በቴሌ ብር ለደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ ከተቋማት ጋር የማስተሳሰር ስራ እየተሰራ በመሆኑ ደንበኞች ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ እየረዳቸው ነው። ከዚህ ቀደም በርካታ የመንግስትና የግል ተቋማት ክፍያቸውን በቴሌ ብር በመክፈል ለደንበኞች ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ክፍያን በቀላሉ በቴሌ ብር መፈጸም የሚያስችል ስምምነት በማድረጉ ደንበኞቹ በኦንል ላይን ሲስተም ተጠቅመው የሰነድ ማረጋገጫ ማግኘት ይችላሉ ብለዋል።

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሙሉቀን አማረ በበኩላቸው፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ክፍያ መፈጸም የሚያስችለንን ስምምነት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ተፈራርመናል ብለዋል። ስምምነቱ የደንበኞች አገልግሎትን ለማሳለጥና ክፍያን ለመፈጸም በየቀኑ ወደ ተቋሙ የሚመጡ ከ7 ሺህ በላይ ደንበኞቹን ሰልፍ በማስቀረት ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። ከዚህ ቀደም ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ብዙ ጊዜን ይጠብቁ ነበር ሲሉም ተናግረዋል።

በቴሌብር መጠቀማችን ህገወጥነትንና ሀሰተኛ ሰነድን ለመከላከል የተዘረጋውን አሰራር ያሳልጣል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አሁን ላይ በኢትዮ ቴሌኮም ይፋ የተደረገው አዲስ አገልግሎት ደንበኞች ጊዜና ጉልበታቸውን ቆጥበው ቀልጣፋና ፈጣን አገልግሎት እንዲያገኙ ይረዳል ብለዋል። የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት እስካሁን ይሰጥ የነበረውን የጥሬ ገንዘብ አገልግሎት በቴሌ ብር አማካኝነት በማድረግ ደንበኛው ሰነዶችን በድረገፅ በመሙላት ያለውን የአገልግሎት መዘግየት ማቃለል እንደተቻለም ገልጸዋል።

ዜና

# የትግራይ የሃይማኖት አባቶች የክልሉን መሪዎች በመገሰጽ ወደሰላማዊ ውይይቱ እንዲመለሱ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ይገባል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የሚገኙ የሃይማኖት አባቶች የትግራይ ክልል መሪዎች ወደ ሰላማዊ ውይይቱ እንዲመለሱ በመምከርና በመገሰፅ አባታዊና መንፈሳዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ሰላማዊ ሂደቱን በመደገፍ ስም ለአገራችን ሰላምና መረጋጋት በማይጠቅም መልኩ የሚደረገውን አሉታዊ እንቅስቃሴ ተቀባይነት እንደሌለውም በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ አባቶች "የሰላም ቅደመ ሁኔታው ሰላም ብቻ ነው!!" በሚል መሪ ቃል በአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ እና አዲስ ዓመትን ምክንያት በማድረግ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ጉባኤው ጦርነቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ከሀገር ሽማግሌ መማክርት ጉባኤ፣ ከታዋቂና ተሰሚነት ካላቸው ገለልተኛ ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለው ጦርነት በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በምክክር እንዲፈታ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ሆኖም ችግሩን በወቅቱ ለመፍታት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ አባቶች በጋራ እና በተናጠል ያደረጉት ጥረት ፍሬ ሳያፈራ ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም ንጋት ላይ ድጋሚ ወደ ጦርነት መግባቱ እንዳሳዘናቸው ገልጸዋል፡፡

መንግሥት አሁንም ጦርነት አቁሞ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዝግጁ መሆኑን እየገለጸ እንደሆነ የጠቀሰው የጉባኤው የበላይ ጠባቂ አባቶች መግለጫ፤ ሕወሓት ጥሪውን እንዲቀበልና ጦርነቱ በአስቸኳይ ቆሞ ወደ ተቋረጠው ሰላማዊ ውይይት እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሕዝባችንን መንፈሳዊ ጥንካሬና ማህበራዊ ትስስሩን ለመሸርሸር፣ የሕዝቦችን አንድነትና፣ ህልውና፣ ለማጥፋት ያለመ እንቅስቃሴ ሲደረግ ነበር ያለው የሃይማኖት አባቶቹ መግለጫ፤ የሀገሪቱን ማደግ የማይፈልጉ በተለይም የህዳሴ ግድብ ግንባታን በማይፈልጉ የውጭ ኃይሎችም ጭምር የተቀነባበረ መጠነ ሰፊ ችግር ሲፈጠር እንደነበር በመግለጫቸው አመላክተዋል።

በዓለም አቀፉ የጦርነት ሕግና መርህ ከወታደራዊ ኢላማ ውጪ የሆኑ የሲቪል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማትና ንፁሀን ዜጎች ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ እንደሚደነግግ ጠቁመው፤ በተጨማሪም ታዳጊ ሕጻናትን ለወታደራዊ ዘመቻ ማሰለፍ ኢ ሰብአዊ እና በዓለም አቀፉ የጦር ሕግ የወንጀል ተግባር መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የደፈረሰውን ሰላም ለመመለስ ጥረት እያደረጉ ለሚገኙ የውጭ አገር መንግሥታት፣ ተቋማትና የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላት ምስጋና ያቀረቡት የጉባኤው የበላይ ጠባቂ አባቶች፤ አሁንም የተቋረጠው የሰላም ውይይት ቀጥሎ ችግሩ በዘላቂነት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ጥረታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል፡፡

በአንጻሩ ሰላማዊ ሂደቱን በመደገፍ ስም ለአገራችን ሰላምና መረጋጋት በማይጠቅም መልኩ የሚደረገውን አሉታዊ እንቅስቃሴ ተቀባይነት እንደሌለውም በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡

ተለዋዋጩ የፖለቲካ እሳቤ ከሕዝብ ማንነት ስለማይበልጥ ኃላፊነት የጎደላቸው ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች የሚደረጉ ንግግሮችንና ቅስቀሳዎችን በምክንያታዊነት መመዘን እንደሚገባ ጠቁመው፤ ከየትኛውም ፓርቲና ፖለቲካ ማህበር ይልቅ የአገርን ዘላቂ ጥቅም በማስቀደም ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባልም ብለዋል፡፡

የተጀመረው ጦርነት እና የሰላማዊ ዜጎች መፈናቀል አብቅቶ አዲሱ 2015 ዓመት የኢትዮጵያውያን መቻቻል፣ ሰላምና አንድነት የሚጠናከርበት መረጋጋት የሰፈነበት እንዲሆንም መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

# ህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለማስቆም እየተሰራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በየአመቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያሳጣ የሚገኘውን ህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ለማስቀረት ከጎረቤት ሃገራት ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

ባለፈው ሳምንት በኅብረት ሥራ ኮሚሽን አዘጋጅነት በተካሄደ የቁም እንስሳት ንግድ ላይ ያተኮረ ዐውደ ጥናት ላይ ፅሁፍ ያቀረቡት በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የግብርና ኢኮኖሚክስ ክፍል ከፍተኛ ተመራማሪ ወይዘሮ ረሂማ ሙሰማ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የሕገወጥ እንስሳት ንግድ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል።

ወይዘሮ ረሂማ፣ ኢትዮጵያ ከቁም እንስሳት ንግድ ማግኘት የነበረባትን የውጭ ምንዛሪ እያጣች መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሁሉም በላይ አስፈሪው ግን የሕገወጥ ንግዱ እንደ መደበኛ የሚቆጠርበት ደረጃ ላይ መድረሱና የተዘረጋው ሥርዓትም ከሕጋዊ ሥርዓቱ በተሻለ መንገድ በእጅጉ የተሰናሰለ መሆኑ ነው ብለዋል።

ለዚህ ደግሞ በድንበር አካባቢ ባሉ የኢትዮጵያና የጎረቤት ሀገራት ዜጎች መካከል የዝምድና ትስስር መኖሩ እንዲሁም የቋንቋና የአኗኗር ተመሳሳይነት መኖሩ የቁም እንስሳት ሕገወጥ ንግዱ በሕጋዊ ሥርዓት ለመምራት እና አጥፊዎችን አግኝቶ ለመቅጣት አስቸጋሪ ሁኔታን ፈጥሯል ይላሉ።

በተጨማሪም ሕገወጥ ነጋዴዎቹ፣ የጉምሩክ ቀራጮች እና ሌሎች ተቆጣጣሪ አካላት በሚያደርጉት ክትትል እንዳይያዙ የሚያስችል የተጠናከረ ድንበር ተሻጋሪ ሥርዓት ከመዘርጋታቸው ሌላ ለመረጃ አቀባዮቻቸው በቀን እስከ 200 ሺህ ብር የሚከፍሉ መሆኑ ችግሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሳንካ ፈጥሯል።

የቁም እንስሳት ንግድ በመጨመሩ የተነሳ በሕግ የማይፈቀዱ እንደ ላም ንግድ ዓይነቶች ሳይቀር እየተለመዱ መሆኑን በጥናታቸው የገለፁት ከፍተኛ ተመራማሪዋ፤ አህያ፣ ፍየል፣ በግና በሬ እንዲሁም ሌሎች የቤት እንስሳት በህገ ወጥ መንገድ እየወጡ ነው። በተለይም የቻይና የአህያ ስጋ ፍላጎት በመጨመሩ በድንበር አካበቢ የአህያ ንግድ ከፍተኛ ሆኗል ብለዋል።

በመንግሥት በኩል ቁጥጥር ለማድረግ ሙከራዎች እንዳሉ በመጥቀስ፤ ሆኖም ከሚያዙት ሕገወጥ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች የማይያዙት በእጅጉ እንደሚልቁ በጥናታቸው ዳስሰዋል። ጥናቱ እንደሚያመላክተውም በሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ላይ በሚደረግ ቁጥጥር ከሚወጡት እንስሳት የሚያዙት አሥር በመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። ለአብነትም እ.ኤ.አ ከ2013/14 እስከ 2020/21 ባሉት ስምንት ዓመታት ውስጥ 78 ሚሊየን ብር የሚገመቱ የቁም እንስሳት ብቻ ናቸው የተያዙት።

በተለይ በሶማሌ እና በጅቡቲ አካባቢ የቁም እንስሳት ንግዱ በከፍተኛ መጠን እየተከናወነ መሆኑ በጥናቱ የተመላከተ ሲሆን ሕገወጥ ነጋዴዎቹ የኢትዮጵያን የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ከሀገር በማስወጣት የሌላ ሀገር ምርት አድርገው ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መላካቸውንም ጥናቱ አመላክቷል። እንደ ጥናቱ ከሆነ፤ በተለይ ፍላጎትን በማጥናት በረመዳንና በአረፋ በዓላት ከፍተኛ የቁም እንስሳት ቁጥር ከሀገር ይወጣል።

ጥናቱ የሕገወጥ የቁም እንስሳትን ወደ ሕጋዊ መንገድ ለመመለስ ብርቱ ትግል የሚጠይቅ መሆኑን በማስገንዘብ የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሄ ሃሳቦችን ጠቁሟል። ከዚህ በፊት ከጎረቤት ሀገራት ጋር የተደረሰው ሕገወጥ የቁም እንስሳት ዝውውር ላይ ያተኮረ ስምምነት መሰረት ይህን ንግድ መቆጣጠር የሚቻለው ቀስ በቀስ ወደ መደበኛው ሥርዓት እያስገቡ በመሄድ ነው የሚለው አንዱ ነው።

ጎን ለጎን የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በዘለለ መልኩ ወደ ሕገወጥ ንግድ የሚወስዱ ተግዳሮቶችን ተከታትሎ መፍታት እንደሚያስፈልግም ተጠቁሟል። የንግድ ሥርዓቱን በማዘመን ሥርዓቱን ወደ ሕጋዊ መመለስ እንደሚቻልም ተነስቷል። ማኅበረሰብ አቀፍ የሆነ የአምራቾችና የንግድ ማህበራት ቢኖሩ እንደረጅም ጊዜ የሕገወጥ ንግድ ማስቆሚያ መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉም ተብሏል።

መድረኩን ያዘጋጀው የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በበኩሉ እንደ ተቋምም ሆነ እንደ ግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋም ጉዳዩ በቀጥታ እንደሚመለከተው በመጥቀስ በሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ ምክንያት የሚደርሰውን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጉዳት ለማከምና የአርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በጥናት የተደገፉ የመፍትሄ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ይገልፃል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፍሬዓለም ሽባባው በበኩላቸው፤ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለማስቆም የበለጠ መደራጀትና መናበብ ተገቢ ነው ይላሉ። ይህ እንደ የትኛውም ዓይነት ስኬት የሚጀምረው ከአንድ እርምጃ በመሆኑ ዐውደ ጥናቱ መዘጋጀቱን ገልፀዋል።

በመንግሥት በኩል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በትኩረትና በተቀናጀ አሠራር መሥራት እንደሚገባቸውና በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያሉ ችግሩን እየተጋፈጡ የሚገኙ ዜጎችንም በማደራጀት መፍታት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

የአርብቶ አደሩን ከእንስሳት ጋር የተቆራኘ የህይወት ዘይቤ እንደካፒታል በመውሰድ ከዘርፉ የሚገኘውን ተጠቃሚነት ማሳደግ እንደሚገባ የተናገሩት ወይዘሮ ፍሬዓለም፤ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ከመንግሥት ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እያገኘ አይደለም። ሆኖም በእንስሳት ምርት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየደገፈ በሚገኝበት ሁኔታ በሕገወጥ የእንስሳት ንግድ እየተፈተነ ነው የሚለውን ሃሳብ ከጥናቱ ግኝት የሚጋሩት ነው።።

በዘርፉ ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል፣ በተደራጀ መልኩ አማራጭ የገበያ ዕድል ከማመቻቸት፣ በሀገሪቱ ድንበር አካባቢዎች የሚካሄዱ ሕገወጥ ንግዶችን ተቆጣጥሮ የተዛባውን የንግድ ሥርዓት ለማረም ሰፊ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ያነሱት ኮሚሽነሯ፤ አሁንም በዘርፉ ሰፊ ውስንነቶች መኖራቸውን ተናግረዋል።

መንግሥት በግብርናው ዘርፍ የአሥር ዓመት ዕቅድ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን በከፍተኛ ደረጃ ለማልማት ማቀዱን የጠቆሙት ወይዘሮ ፍሬዓለም፣ አካባቢዎቹ ከዚህ በፊት ተገቢውን ትኩረት እንዳላገኙ ገልፀው፤ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ባለፉት ጊዜያት እንደ ኋላ ቀር ከመታየታቸው ባሻገር እርዳታ ፈላጊዎች ብቻ ሆነው ይወሱ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን መንግሥት የኢኮኖሚ መሠረት መሆናቸውን አምኖ እየሠራ ነው ብለዋል።

ያሉት ችግሮችም ሰፊ በመሆናቸው ተፈላጊውን ለውጥ ማምጣት አለመቻሉን ተናግረዋል። የቁም እንስሳት ንግዱን ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ለማስገባት ጠቁመው፤ ሆኖም በአካባቢዎቹ የመንገድ፣ ሎጅስቲክስ፣ የርቀትና የተዛባ የንግድ ሥርዓት እንዲሁም የሌሎች ችግሮች ሰለባ መሆናቸውን አብራርተዋል።

የመሰረተ ልማት ችግሮችን ጨምሮ ሌሎች ንግድ ሥርዓት ችግሮች በጥናቱ መሰረት የሚመለሱ መሆናቸውንና በተለይም ግን ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመዋል። በቅንጅታዊ አሠራር ለመፍታትም በዐውደ ጥናቱ የሚመለከታቸው አካላት መገኘታቸውንና የድርሻቸውን በመወጣት ያለው ችግር ሊፈታ ይችላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማኅበር ወይዘሮ ክብሬ ሙላት በበኩላቸው፤ በዘርፉ አሁን ባለው ደረጃ ለውጥ ሊመጣ የሚችልባቸው ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ገልፀዋል።

የቁም እንስሳት ሕገወጥ ንግድን ለመከላከል ንግድ ሚኒስቴርና ግብርና ሚኒስቴር በቅንጅት እየሠሩ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በንግድ ሚኒስቴር በኩል ለቁጥጥር የሚያመቹ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን አብራርተዋል።

እንደ ወይዘሮ ክብሬ ገለፃ፤ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ በመሥራቱ ሕገወጥ ነጋዴዎች እየተያዙ በመሆኑ ተስፋ ሰጪ ጅምሮች እየታዩ ነው። ከዚህ ቀደም ሕጋዊ አስመለስሎ የቁም እንስሳትን ከሀገር የማስወጣት ነገሮችም ቆመዋል። የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ከመንግሥት ጋር በጥምረት እየሠሩ ነው። ከዚህ በፊት በመንግሥት በኩል አልተተገበሩም እየተባሉ አቤቱታ ሲስተናገድባቸው የነበሩ ችግሮች እየተፈቱ ነው።

ኢትዮጵያ በለውጡ ማግስት ጀምሮ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለማስቆም ከጎረቤት ሀገራት ጋር በታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት የተመሩ ተደጋጋሚ ውይይቶችን አድርጋለች። በተጨማሪም ዘርፉ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲያመጣ ለማስቻል አዲስ ፖሊሲ ቀርፃ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች።

# መንግስትን ከአሸባሪ ድርጅት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጦርነት ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል። አሸባሪው ሕወሓት የሰብአዊ እርቅ መንፈስን እየጣሰ ጥላቻን በመስበክ፤ ህጻናትን ለውትድርና በመመልመልና የህዝብ ቅስቀሳ በማድረግ ለሌላ ዙር ግጭት ጦርነት ቀስቅሷል።

የፌዴራል መንግስት በኢትዮጵያ ያለውን ተጨማሪ ጥቃት ለማስቆም የሚያደርገውን ጥረት የሚደግፉ ሀገራትን አመስግነው አሁንም ለሕወሓት ድጋፍ የሚሰጡ አንዳንድ ቡድኖች እንዳሉ ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል። ሚዛናዊነትን ከሳተ ድርጊታቸው እንዲታረሙም ጥሪ አቅርበዋል።

በአማራና አፋር አካባቢዎች የጀመረው የሕወሓት የቅርብ ጊዜ ጥቃት ተቀባይነት እንደማይኖረው ገልፀው፤ ዜጎች የሽብር ቡድኑ ሰለባ እንዳይኑ መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ መንግስት በአሸባሪው ቡድን ላይ በሚወስደው እርምጃ በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ እራሱን ለመከላከል ከወታደራዊ ተቋማት እንዲያርቅ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ ቆይቷል ብለዋል።

በተሳታፊዎቹ በኩል የኢትዮጵያ መንግስት ለሠላም ሲያደርግ የነበረውን ጥረት አሁንም እንደሚያደንቁ መግለጻቸውን የሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስዓለም ለጋዜጠኞች ተናግረዋል። ከዲፕሎማሲው ማህበረሰብ ጋር የተደረገው ውይይትም ፍሬያማ እንደነበር ገልጸዋል።

# ሕወሓት ወረራውን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ያለው ሕዝብን ከረሃብ የማዳን ግዴታ ስላለበት ጭምር መሆኑንም አክሎ ገልጿል።

መግለጫው፣ በሕወሓት የሽብር ቡድን እየደረሱ የሚገኙ ጥፋቶችን ለማስቆም መንግሥት ለሰላማዊ አማራጭ ያደረጋቸው ጥረቶች ሁሉ እየመከኑ ባሉበት ሁኔታ፤ አሸባሪውን ሕወሓት መጫን ሲገባቸው "ሁለቱም ወገኖች" በሚል የሚወጡ መግለጫዎች ከእውነታው ያፈነገጡ በመሆናቸው ተቀባይነት እንደሌላቸው በመግለፅ፤ ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም አማራጮችን በመግፋት የከፈተው ጥቃት ሃገራችንን እንዳይበትን፣ የመከላከያ ኃይላችን በሁሉም አቅጣጫ የተከፈተበትን ወረራ ከሰላም ወዳዱ ደጀን ሕዝብ ጋር በመሆን በጽኑ ጀግንነት በመከላከል ላይ ይገኛል ብሏል።

ሕወሓት በመንግሥት በኩል የቀረቡ ተደጋጋሚ የሰላም አማራጮችን ችላ በማለት ለሦስተኛ ጊዜ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ባደረገው ትንኮሳ ጦርነት ካገረሸ አንድ ሳምንት አልፎታል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## «ሁለቱም ወገኖች» በሚል የሚወጡ መግለጫዎች ከእውነታው ያፈነገጡ እና ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው

አሸባሪው ሕወሓት በሕዝባዊ እንቢተኝነት ከስልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ መንግሥት ከቡድኑ ጋር የተፈጠረውን አለመግባባት በድርድር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የተለያዩ ጥረተቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። ለሰላማዊ የመንግሥት ሥርዓት ሽግግር ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ በተግባር አሳይቷል።

ከቡድኑ ጋር የተፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት የአገር ሽማግሌዎችን ወደ ክልሉ ከመላክ አንስቶ፤ እናቶች በጉዳዩ ዙሪያ ጣልቃ እንዲገቡ በማድረግ ቡድኑ ሰላምና የሰላም አማራጮችን እንዲቀበል ረጅም ርቀት ተጉዟል። በዓለም አቀፍ ደረጃም በቡድኑ ላይ ጫና ለማድረግ ሞክሯል።

ሰላም በአንድ አካል በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ባለመሆኑ መንግሥት ብዙ የደከመበት የሰላም መንገድ በአሸባሪው ሕወሓት የእብሪትና የኃይል አምላኪነት ፍጥረታዊ ባህሪው፤ በታሪካዊ ጠላቶቻችን ግፊት የተነሳ ፍሬ ሊያፈራ አልቻለም።

መንግሥት ስለሰላም እያዜመ፤ የሰላም አማራጮችን ከፍ አድርጎ እያስተጋባ፤ አሸባሪው ሕወሓት ሁሉንም ሰላም አማራጮች ረግጦ የትግራይን ሕዝብ ለአመታት በቀበሮ ጉድጓድ ተቀምጦ ሲጠብቅ በነበረው የአገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ከኋላ ጥቃት በመሰንዘር ለሰላምና ለሰላም አማራጮች ምንም ዓይነት ቦታ እና ደንታ እንደሌለው በአደባባይ አሳውቋል።

«ከአማራ ሕዝብ ጋር የማወራርደው ሂሳብ አለኝ» በሚልም መንግሥት ከትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የቀረበለት ከትግራይ የመውጣት ጥያቄ ተቀብሎ በወጣ ማግስት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ጀሌዎችን አሰልፎ በአማራና በአፋር ሕዝቦች ላይ ወረራ በማካሄድ ይህ ነው ተብሎ ሊዘረዘር የማይችል ግፎችን ፈጽሟል።

ከፍጥረቱ ጀምሮ ለሰላምና ለሰላም አማራጮች ቦታ ኖሮት የማያውቀው ይህ አሸባሪ ቡድን፤ በመንግሥት ኃይሎች ለሁለተኛ ጊዜ አከርካሪው ተሰብሮ ወደ መጣበት ከፍ ባለ ውርደት በተመለሰ ማግስት መንግሥት የትግራይን ሕዝብ ታሳቢ ያደረገ የተናጠል የተኩስ አቁም አድርጓል። አለመግባባቶች በውይይት እንዲፈቱ ያሉትን አማራጮች በሙሉ ለመጠቀም ሞክሯል።

ጉዳዩ ገለልተኛ በሆነው በአፍሪካ ህብረት በኩል እንዲታይ ፈቃደኝነቱን ከመግለጽ ባለፈ፤ የህብረቱ ተልዕኮ እንዲሳካ ብዙ ርቀት ተጉዟል። በሰላም ንግግሩ የሚሳተፈውን ኮሚቴ ከማዋቀር አንስቶ የኮሚቴ አባላቱን ይፋ በማድረግ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት አረጋግጧል።

አሸባሪው ሕወሓት ግን መንግሥት የዘረጋቸው የሰላም እጆች ላለመቀበል ቅድመ ሁኔታዎችን ሲደረድር፤ ለአፍሪካ ህብረት የሰላም ንግግር ተደራዳሪ በመሰየም ራሱን ዝግጁ ከማድረግ ይልቅ የሰላም ንግግሩ ቴክኒካሊ ፈርሷል ሲል ተደምጧል፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ ቡድኑ መንግሥት የዘረጋውን የሰላም አማራጮች ሁሉ ረግጦ ለሦስተኛ ጊዜ በአገሪቱ ላይ ጦርነት አውጆ ወደ ጦርነት ገብቷል። በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥትን ወደማፈልጉት ጦርነት እንዲገቡ አስገድዷቸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በየዘመናቱ በጦርነት ምክንያት ከከፈሉት ዋጋ አንጻር መቼም ቢሆን ለውስጥ ችግሮቻቸው ጦርነት የችግር መፍቻ ቁልፍ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት የላቸውም፤ በዚህ መንገድ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለመክሰስ መሞከር በብዙ መልኩ ተጠየቅ የሚጎድለው ነው።

ይህ ማለት ግን የአገርና የሕዝብን ህልውና ሰላምና ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚከትን የትኛውንም ስጋት ቁጭ ብለው ይመለከታሉ ማለት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብ፤ መንግሥትም እንደ መንግሥት አገርን እንደአገር የመታደግ ሕገመንግሥታዊ ፤ የዜግነትና የሞራል ግዴታ አለባቸው። ዛሬ ላይ እያደረጉ ያለውም ይህንኑ ነው ።

በአሁኑ ወቅት አሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን ገፍቶ በየአቅጣጫው በለኮሰው እና ዛሬም እያስፋፋ ባለው እሳት ንጹሐን እየተገደሉ ነው፣ ሕዝብ እየተፈናቀለ፣ ንብረትም እየወደመ ነው። ይህንን የቡድኑን ከአገር አጥፊነት ተግባር ማስቆም የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ኃላፊነት ነው ።

የሽብር ቡድኑ ሰላማችንን እንዳያደፈርስና አገራችንን እንዳያፈርስ ፤ ወደ ትግራይ የሚላከውን ርዳታ ለተቸገረው ሕዝብ እንዲደርስና ትግራይ ውስጥ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ሕዝቡን ከችግር ለመከላከል፤ ቡድኑ ሕዝብን በረሃብ ለመቅጣት ዐቅዶ ተደጋጋሚ ጦርነት የሚከፍተው በክረምት የግብርና ወቅት በመሆኑ መንግሥት ወረራውን እየተከላከለ ያለውን ሕዝብ ከረሃብ የመታደግ ግዴታ አለበት።

ብዙ ጥፋቶችን አምጦ የሚንቀሳቀሰውን አሸባሪ ቡድን ከዚህ በኋላ እድል መስጠት፤ አገርን እንዲያፈርስ ፤ሕዝብን ለከፋ መከራና ስቃይ አሳልፎ የመስጠት ያህል ነው ። ይህን ደግሞ የየትኛውም አገር ሕዝብና መንግሥት የሚፈቅደው አይደለም። እኛም ኢትዮጵያውያን ለዚህ ዓለም አቀፋዊ እውነታ የተገዛን ነን ።

ይህንን ተጨባጭ አደባባይ የሞላ እውነታ ወደ ጎን በመተው የተለያዩ ወገኖች አሸባሪውን ሕወሓት ከጥፋት መንገዱ እንዲመለስ ጫና ከማድረግ ይልቅ «ሁለቱም ወገኖች» በሚል የሚያወጧቸው መግለጫዎች ከእውነታው ያፈነገጡ እና ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው።

መንግሥት አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት ከጅምሩ አንስቶ የሄደባቸውን የሰላም መንገዶች ከግምት ያላስገባ፤ ስለ ሰላም የከፈላቸውን ዋጋዎች ያላገናዘበ፤ አሸባሪው ቡድን በጀመረው የጥፋት መንገድ እንዲቀጥል ተጨማሪ አቅም የሚሰጠው ነው።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የዶክተሩ የመጨረሻው የኃላፊነት ዝቅጠት …

ዘካርያስ ዶቢ

ኢትዮጵያ ልጆቿ በዓለም አቀፍ፣ በአህጉራዊ እና ክፍለ አህጉራዊ ተቋማት፣ መድረኮች፣ ወዘተ አንጻባራቂ ሆነው እንዲታዩ ጽኑ ፍላጎት አላት:: የልጆቿ በእነዚያ ተቋማት፣ መድረኮች፣ ወዘተ መታየት የእሷም መታየት ነውና እምነቷ ትክክል ነው::

ይህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዲፈጠር አገሮች አጥብቀው ይሠራሉ፤ ይህን አጋጣሚ ማባከን የሚፈልግ አገር የለም፤ የአገራቸው ጥቅም ማስጠበቂያና ገጽታ መገንቢያ፣ የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸው ማጠናከሪያ፣ ወዘተ አድርገው ይጠቀሙበታል:: አይደለም የዓለም አቀፍ ድርጅት መሪ በእነዚያ ታላላቅ ተቋማት የሚገኝ ተራ ሠራተኛም ቢሆን፣ ለአገርና ሕዝብ ያለው ፋይዳው ከፍተኛ ነው::

ለእዚህም ሲባል አገሮች ብቻም ሳይሆኑ አህጉራትና ክፍለ አህጉራት የራሳቸው ሰው በዓለም አቀፍ ድርጅቶች መሪነት ስፍራ ላይ እንዲቀመጥ ሲሉ ብዙ ዋጋ ይከፍላሉ:: በየአገሮቹ በመዘዋወር የምረጡኝ ቅስቀሳ ያደርጋል:: ለሎቢስቶች (አግባቢዎች) ከፍተኛ ገንዘብ እየተመደበ ይህ ሥራ እንደሚካሄድ ይነገራል:: ለዚህ የሚከፈለው ዋጋ ለአገር ለአህጉርና ክፍለ አህጉር ሲባል የሚደረግ ነውና ተገቢ ነው::

ኢትዮጵያም የዓለም ጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም ለዓለም ጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተርነት ዕጩ ሆነው በቀረቡ ጊዜ እንዲመረጡላት ብዙ ደክማለች:: ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ህብረት አገሮችም ይህንኑ አድርገዋል:: ለእዚህም ሎቢስቶችን ለመቅጠርና ለመሳሰሉት ብዙ ዋጋ እንደከፈለች በወቅቱ ሲነገር ነበር:: የአፍሪካ አገሮች ድምጽ ከጎናቸው እንዲቆም በአህጉሪቱ የተለያዩ አገሮች በመዘዋወር ብዙ ተሠርቷል:: ይህ መሆኑ ትክክል ነው::

በዚያን ወቅት በዶክተር ቴድሮስ ላይ በአገር ውስጥ ከኤችአይኤድስ ኪት ግዥ ጋር በተያያዘ ቅሬታ የሚያሰሙ አካላት እንደነበሩ አስታውሳለሁ:: ያ ቅሬታ ጠንካራ መረጃዎች ያሉት ሆኖም፣ በግዥው የአገር ሀብት ተመዝብሯል እየተባለም፣ ዶክተሩ ለዓለም ጤና ድርጅት እንዳይወዳደሩ ሆን ተብሎ የታቀደ ተግባር ነው ተብሎ ሳይስተናገድ ቀርቷል ይባላል::

ዛሬ ላይ ቆመን ስንመለከተው ደግሞ በወቅቱ በአገሪቱ አድራጊ ፈጣሪ የነበረው አሸባሪው ትህነግ አግባቢዎችን (ሎቢስቶችን) ለማሰማራት አያሌ የኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ እንዲወጣ አድርጓል ይባላል:: ለዚህ ታስቦ ከሆነ ይህም ባልከፋ:: ለማናቸውም ተብሎ ከሆነ ግን በእጅጉ ያንገበግባል:: እንደ አገርና አህጉር ሰውዬውን የዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊነት ላይ ለማስቀመጥ የተደረገው ርብርብ የሚደነቅ ነው::

ያ ሁሉ ተደክሞም ዶክተር ቴድሮስ የዓለም ጤና ድርጅት ዋና ኃላፊ ተደርገው ተመረጡ:: ዶክተሩ ለኢትዮጵያ ምን ዋሉላት ተብሎ ሲታሰብ ግን ያሳዝናል:: የዋለላቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እጅ ነክሰው፣ አገሪቱን ለማፍረስ ከሚጣጣረው አሸባሪው ትህነግ ጋር ሆነው እየሠሩ ናቸው:: የኢትዮጵያን አጀንዳ ከፍ አድርገው ያሳያሉ፣ የኢትዮጵያን ገጽታ ይገነባሉ የተባሉት ዶክተሩ፣ ኢትዮጵያውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ እየጨፈጨፈ ካለው ቡድን ጋር ሆነው መሥራታቸውን ቀጥለውበታል:: የቡድኑ ቃል አቀባይ እስኪመስሉ ድረስ ።

አጀንዳቸው ሁሉ የአሸባሪው ትህነግ ጉዳይ ሆኗል:: ቡድኑ እንደሚያደርገው የትግራይ ሕዝብ በረሃብ አደጋ ውስጥ ነው፣ የመንግሥት ኃይሎች ትግራይ ውስጥ የዘር ጭፍጨፋ አካሄዱ፣ መሠረታዊ አገልግሎት ተቋማት ባለመኖሩ ሳቢያ ከቤተሰቦቼ ጋር መገናኘትም ሆነ ገንዘብ ልልክላቸው አልቻልኩም፣ ወዘተ እያሉ መክሰሳቸውን ቀጥለዋል::

ቡድኑ በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች የሚገኙ የኢትዮጵያ ሕፃናት፣ እናቶች፣ አዛውንቶች በአጠቃላይ ሕዝቦች ጉዳይ ለዶክተሩ ጉዳያቸው አይደለም፤ የአማራ ክልልና አፋር ክልሎችን ያን ያህል ወርሮ ባሰቃየበት ወቅት፣ እነዚያ ሁሉ ንጹኃን ኢትዮጵያውያን በጅምላ ጭፍጨፋ ሲገድሉ ዶክተሩ የተነፈሱት የላቸውም፤ እነዚያ ሁሉ የጤና ተቋማት ሲፈርሱ፣ ሲዘረፉ ለእሳቸው ምናቸውም አልነበረም:: በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች የክረምት ዶፍ በሚወርድበት ወቅት ከቀዬቸው ተፈናቅለው በየድንኳኑና በየትምህርት ቤቱ ተጠልለው አሳራቸውን ሲያዩ ያሉት አልነበራቸውም::

በአሸባሪው ትህነግ ተላላኪዎች እነ ሸኔ በመላ ኦሮሚያና በአንዳንድ የአማራ ክልል አካባቢዎች ስንትና ስንት ንጹኃን ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ ሲጨፈጨፉ እሳቸው ያሉት የለም:: ዝምታቸው የቡድናቸውን ድል እያጣጣሙ ነው ያሰኛቸዋል::

ቡድኑ በሚሠራቸው ድራማዎች በቀጥታ በመተወን የትግራይ ሕዝብ ተራበ፣ መድኃኒት አጣ፣ መሠረተ ልማት ፈረሰበት፣ ስልክ ባንክ መብራት ውሃ ተቋረጠበት ሲሉ ነው የሚሰሙት:: መሠረተ ልማት አውዳሚው፤ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዳይቀርቡ ዋነኛው እንቅፋት ትህነግ መሆኑን ስረ መሠረቱን ጠቅሰው ትንፍሽ አላሉም፤ ጦርነቶቹን ሁሉ የሚጀምራቸው እሱው እንደሆነም እያወቁ የጦርነት ጀማሪው የኢትዮጵያ መንግሥት ነው ከሚለው ቡድን ጋር መወዛወዛቸውን ቀጥለዋል::

የእናት አገርን ውለታ መካድ ይሏል እንዲህ ነው:: ያነረሰን እጅ መንከስ ማለት እንዲህ ነው:: ሰውየው ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላት መሆን ይሆንላቸው አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ነው:: በታላቅ ዓለም አቀፍ ኃላፊነት ላይ ተቀምጦ በለውጡ ላይ አኩርፎ ትግራይ የመሸገውን ትህነግ መደገፍ ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላት መሆን ነው::

አገራቸውን በአጠቃላይ አፍሪካን በተለያየ መልኩ ፕሮሞት ያደርጋሉ፤ ተጠቃሚም ያደርጋሉ ተብለው የተጠበቁት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ኢትዮጵያን ካላፈረስኩ እያለ ለሚደክመው ቡድን፣ በሰው ልጅ ላይ አሰቃቂ የተባሉ ግድያዎች እየፈጸመ ያለው ትህነግ ዋና ቃል አቀባይና ጠበቃ ሆነው እየሠሩ ናቸው:: ዓለም በአደራ የሰጣቸውን የዓለም ጤና ድርጅትነት ታላቅ ቦታ የአሸባሪው ትህነግ ቃል አቀባይ ቢሮ አድርገውታል:: የሚመሩት ድርጅት በእሳቸው መጥፎ ተግባር የተነሳ በዓለም ጤና ድርጅት የሕወሓት ቢሮ ቢባል አያስኬድም ተብሎ አይታሰብም:: እኔ ያስኬዳል እላለሁ::

በግላቸው ቡድኑን ቢደግፉ ብዙም ችግር ላይኖረው ይችላል ተብሎ ይታሰብ ይሆናል:: ከያዙት ቦታ እና አሸባሪ ቡድኑ በሰው ልጅ ላይ እያደረሰ ካለው እኩይ ተግባር አኳያ ሲታይ ግን ይህን ቡድን ደግፈው ሽንጣቸውን ገትረው ከጎኑ መቆማቸው በእጅጉ ኃላፊነት የጎደላቸው ያሰኛቸዋል::

ቡድኑ መንግሥትን በኃይል ለመጣል የሞከረ፣ የአገርን ሉአላዊነት ለአመታት ሲያስጥብቅ የኖረውን የሰሜን እዝ በመካድ ከጀርባው የወጋ ጨፍጫፊ ነው፤ ሕፃናትን እናቶችን አቅመ ደካሞችን የሚጨፍጨፍ የሚያስጨፈጭፍ እንደመሆኑ ከዚህ ቡድን ጋር ላይ ታች ማለት በራሱ ከጨፍጫፊዎቹ፣ ከከሀዲዎቹ፣ ያስመድባል::


አብረኸው የምትውለው የምታድረው ሰው፣ አብረኸው የምትሠራው ሰው አገር እያወከ ያለ ከሆነ ከእሱ ጋር የሚኖርህን ግንኙነት በልኩ ማድረግ የግድ ነው:: አለበለዚያ ከኑግ ጋር የተገኘ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ ይመጣል፤ እያወቁ የሌባ ዕቃን ማስቀመጥ ወይም ለሌባ መንገድ መምራት ሌባ አያሰኝም ተብሎም አይወሰድም:: እያወቁ አብሮ መስረቅ ውስጥ ከተገባ ደግሞ ሙልጭ ያለ ሌባ መሆን ነው::

ጓዶቻቸው ኢትዮጵያ መፍረስ አለባት፤ እናፈርሳታለን ይላሉ፤ እሳቸውም ኢትዮጵያውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ ሰጨፈጭፉ ከማውገዝ ይልቅ ጭፍጨፋው የተፈጸመው በመንግሥት ነው እያሉ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንዲጥል ሌላም ሌላም እርምጃ እንዲወሰድ ሲወተውቱ ከቆዩት መካከል ናቸው፤ አሁንም እየወተወቱ ናቸው:: በትግራይ ለተፈጠረው ቀውስ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂው ትህነግ ሆኖ ሳለ እሳቸው ትህነጎች በሀሰት የሚያሰራጩትን መረጃ ይዘው መንግሥትን መክሰስን ሥራቸው አድርገውታል::

የዓለም ጤና ድርጅትን እየመሩ ለአንድ አሸባሪ፣ ጦረኛና ገዳይ ቡድን በመወገን ነጋ ጠባ የሚያሰራጩት መረጃ ያን ትልቅ ተቋም የአሸባሪ ትህነግ ቅርንጫፍ ቢሮ የማድረግ ያህል ነው:: እውነታው የተቋሙን የመተዳደሪያ ቻርተር የሚጻረር፣ የሰውየው የኃላፊነት መገዘቀ የቱን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ጭምር ነው::

# በአባይ ላይ የጀገነ እድለኛና ባለድል ትውልድ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)



ሰው ብዙ ተፈጥሮ አለው..ከዛኛው አለም ወደዚህኛው አለም ሲመጣ ለራሱና ለሌሎች ታሪክ ሰርቶ እንዲያልፍ ነው:: የሰው ልጅ አቅሙን፣ ሀይሉንና ተፈጥሮውን መጠቀም ከቻለ ታሪክ የማይሰራበት ምንም ምክንያት የለም:: ታሪኮቻችን የተቀመጡት በእኛ የማሰብ አቅምና የማድረግ ሀይል ውስጥ ነው:: ታሪክ መስራት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብርቃችን አይደለም:: በተለያየ ጊዜ አለምን ያስደነቁ፣ ከሰው ልክ አቅም በላይ የሆኑ በርካታ ታሪኮችን ሰርተናል:: አሁንም እየሰራን ነው::

ለአብነት ብንጠቅስ እንኳን የአድዋ የድል ታሪክ አለም የሌለው፣ ለአፍሪካውያን ብርቅ የሆነ የእኔና የእናተ የጋራ ታሪካችን ነው:: በተለያዩ ጊዜ፣ በተለያየ ቦታ አባቶቻችን በአንድነትና በህብረት ታሪክ ሰርተዋል:: ዛሬ ላይ በክብር የምንጠራባቸውን እልፍ የኲራትና የሞገስ ታሪኮችን አስረክበውናል:: የአባቶቹን የጽናት ክንድ የወረሰው ይሄኛው ትውልድ ደግሞ በአባይ ላይ ጀግኖ እንሆ የአባቶቹን ህልምና ምኞት እውን አድርጎታል:: ይሄ ትውልድ እኔና እናተ ነን..ይሄ ትውልድ በመቻል፣ በማድረግ፣ በማሸነፍ የተካነ የአባቶቹ የጽናት ጽንስ የጸነሰው ትውልድ ነው::

ሀገርና መንግስት ከግለሰብ የሚጀምሩ የብዙሀን ስፋት ናቸው:: ሀገር ራዕይ እንዳለው ትውልድ፣ ራዕይ እንዳለው መሪ፣ ራዕይ እንዳለው ዜጋ የሚባርከት የለም:: አሁን ላይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ራዕይ ባላቸው መንግስትና ህዝቦቿ እየተባረከች ነው :: ይሄን እውነት ከሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ውስጥ ሁለቱን መዝዤ ላውጋችሁ:: መነሻዬ በአባይ ላይ ስለጀገኑ እድለኛና ባለ ድል ትውልዶች ነው:: ታላቁን የህዳሴ ግድብ ተንተርሼ ስለዚህ ትውልድ እድልና ድል ላውጋችሁ::

እንደሚታወቀው ይሄ ትውልድ ቁጭት የነቀነቀው፣ የአባቶቹን አደራ ውስጡ አኑሮ እድልና ድልን በመጠበቅ የሚንቀሳቀስትውልድ ነው:: ከስንት አንድ ጊዜ ካልሆነ ብዙ ጊዜ እድልና ድል አንድ ላይ አይመጡም:: ሲመጡ ግን ሌላ ናቸው..ትውልዱን ባለታሪክ፣ ህዝቡን ባለማዕረግ ነው የሚያደርጉት:: እድልና ድል በአንድ ላይ ሲመጡ ተዐምር ነው ። የሚፈጥሩት..ታሪክ ነው :: ይሄኛው በአባይ ላይ የገነነው የእኔና የእናተ ትውልድ እድልና ድል በአንድ ላይ የመጡለት ትውልድ ነው::

በዚህ ትውልድ አብራክ ስር እንደ መብቀል ኲራትና ሰውነት አለ ብዬ አላስብም:: በሁለት ተርባይንና ጀነሬተሮች )ይሄ ትውልድ ታሪክ ከመስራት ባለፈ የአባቶቹን እውነት፣ የያኔውን ትውልድ ምኞት የመለሰ ትውልድ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ በሶስተኛው የውሀ ሙሌት ስነስርዐት ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት ላይ በአባይ ላይ የጀገነውን ይሄኛውን ትውልድ ‹እድለኛና ባለ ድል ትውልድ› ሲሉ ነበር የገለጹት::

አያይዘውም ‹አባይ ሲገደብ እንደማየት፣ ሲፈስ እንደማየት፣ በእጅ እንደመዳሰስ ፣ ኃይል ሲያመነጭ እንደማየት እድለኝነት አለ አልልም:: ይሄ ትውልድ እድለኛና ባለ ድል ትውልድ ነው› ነበር ያሉት:: እውነት ነው የዚህ ትውልድ አንድ አካል ሆኖ በአባይ ላይ እንደመጀገን እድለኝነት አለ አልልም:: የጥንት አባቶቻችን አባይን ገድበው ኃይል የማመንጨት ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው:: ግን እድል አልነበራቸውም:: ግድቡን ገድቦ ኃይል እንዲያመነጭ የሚያደርግ እውቀትና ቴክኖሎጂ፣ የተማረ የሰው ኃይልም አልነበራቸውም:: ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የግድቡን ወጪ የሚሸፍን የፋይናንስ አቅም እልነበራቸውም::

ከእኔና ከእናተ በፊት ያሉት አባቶቻችን ልክ እንደቀደሙት ሁሉ አባይን ከመገደብ ባለፈ ህልምና ምኞታቸውን እውን የሚያደርጉበት ምንም አጋጣሚ አልነበረም:: አንድ ነገር በተፈለገው መልኩ ውጤት እንዲያመጣ እድልና ድል ግድ ይሉታል:: እድል ወደ ድል የሚወስድ ጎዳና ነው:: በሰዐቱ አባቶቻችን እድላቸውን እንዳይጠቀሙና ወደ ድል እንዳይቀይሩት ሳንካ ተፈጥሮባቸው ነበር::

የግብጽና የአንዳንድ ምዕራባውያን ክፋትና ራስወዳድነት ታክሎበት አባይ ሳይገደብ በምኞት ብቻ እንዲቀር ሆነ:: አባይ ግን አልሞተም በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ በቁጭትና በሀሳብ ነበር:: በዘፈንና በግጥም፣ በፉከራና በቀራርቶ እየተሰደበና እየተገላመጠ፣ እየተናቀና እየተወደሰ መኖሩን ቀጠለ:: አባቶቻችን አርግዘው ሳይወልዱት ለእኛ አደራ ብለውን አለፉ:: እንሆ አባይ ተንከባሎ እድለኛውና ባለድሉ ትውልድ ላይ ደረሰ:: እንሆ በኢትዮጵያውያን የተባበረ ክንድ አባይ ተሞሸረ:: እኛም እልል አልን::

**አባይ በብዙ ልዩነት ውስጥ አንድነትን የሰጠን ፣ በብዙ መለያየት ውስጥ ያስተቃቀፈን ጽናታችን ነው:: ከአድዋ ቀጥሎ የተከሰተ የትውልድ ክስተት ነው:: ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ ምንም ማድረግ እንደሚችሉ ለአለም ያሳዩበት፣ ጠላቶቻችንን አንገት ያስደፋንበት የክብራችን ማህተም ነው**

አባይ ጎጃ ወጥቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ከድህነትና ከኋላቀርነት ሊያወጣ እንሆ ከነግርማ ሞገሱ እየደነፋ ነው:: ተጠናቆ እልል የምንልበት ጊዜ የሁላችንም የዳግም ትንሳኤ ቀን እንደሚሆን አምናለው:: እስከዛው ግን እንደ አይናችን ብሌን፣ እንደ ህልውናችን መሰረት እንጠብቀዋለን። ምክንያቱም አባይ ማለት ከግድብ ባለፈ የአንድነታችን ምስክር፣ ከኃይል ማመንጨት ባለፈ የወንድማማችነታችን ካርታ ነውና::

አፋፍ ላይ ነን..በአባይ ልንስቅ..በአባይ መከራችንን ልንረሳ:: በአባይ የልፋታችንን ልንበላ፣ የአንድነታችንን ውጤት ልናይ:: በአሁኑ ወቅት የግድቡ የሲቪል ስራዎች ግንባታ ዘጠና አምስት ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን ሌሎች ተያያዥ ስራዎች እንዳሉ ሆነው አጠቃላይ አፈፃፀሙ ደግሞ ሰማኒያ ሶስት ከመቶን የዘለለ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህም መሰረት በያዝነው አመት የህዳሴ ግድቡ ካሉት አስራ ሶስት ተርባይኖች በሁለት ዩኒት (በሁለት ተርባይንና ጀነሬተር ) ኃይል ማመንጨት እንዲጀምር የማድረግ ስራው ተጠናቆ በሁለት መቶ ሰባ አምስት ሜጋ ዋት ታላቁ የህዳሴ ግድባችን ኃይል ማመንጨት ጀምሯል::

አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ስራ በሁለት አመት ውስጥ እንዲጠናቀቅ እየተሰራ ሲሆን በቀጣይ አመታት ውስጥ አባይ አልቆ ሙሉ በሙሉ ኃይል ወደማመንጨት ሲሸጋገር ከእድገትና ከስልጣኔ ባለፈ ደስታችንን በጋራ የምንቋደስበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም:: እስከዛው የቀሩትን ጥቂት አመታት በተለመደው አንድነትና ፍቅር በተባበረ ክንድ ትንሳኤውን እውን ማድረግ ይጠበቅብናል::

አባይ በብዙ ልዩነት ውስጥ አንድነትን የሰጠን ፣ በብዙ መለያየት ውስጥ ያስተቃቀፈን ጽናታችን ነው:: ከአድዋ ቀጥሎ የተከሰተ የትውልድ ክስተት ነው:: ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ ምንም ማድረግ እንደሚችሉ ለአለም ያሳዩበት፣ ጠላቶቻችንን አንገት ያስደፋንበት የክብራችን ማህተም ነው:: ከአድዋ ቀጥሎ ትውልድ የሚዘክረው የዚህኛው የእኔና የእናተ ሀቅ ነው:: ኢትዮጵያ የምትጠራበት የዚህኛውና የዚያኛው ትውልድ እልፍ የታሪክ ጌጥ ያላት ቢሆንም:: አባቶቻችንን ስናስብ አድዋን ይሄኛውን ትውልድ ስናስብ ደግሞ የህዳሴ ግድባችንን እናስታውሳለን::

ትውልድ ሁሌም ታሪክ እንደሰራ ነው:: የታሪክ ማብቂያ መለያየት ነው:: ሀገር ትውልድ ብኩን የሚሆኑበት አንድ አጋጣሚ ቢኖር መለያየት..መገፋፋት ነው:: ትውልድ በአንድነት ከቆመ ሁሌም ታሪክ አለው:: ሁሌም ታሪክ መስራት ይችላል:: አድዋም ሆነ አባይ የምንም ሳይሆን የአንድነታችን ሚስጢር ነው:: አሁንም በአንድነት ቆመን እንደ ህዳሴ ግድባችን አይነት ከድህነትና ከኋላቀርነት ከልመናም ሊያወጣን የሚችል የእድልና የድል አሻራችንንእናሳርፍ ::

በአባይ ጉዳይ ላይ የግብጽና የሱዳን የሌሎች ምዕራባውያን ተጽዕኖ ምን ያክል እንደነበር እናውቀዋለን:: በአንድነት መክተን አሸነፍነው እንጂ ተለያይተን ቢሆን ኖሮ አባይን በዚህ ልክ አናየውም ነበር:: ጠላቶቻችን መቼም የእኛን ደስታ፣ የእኛን ሳቅ፣ የእኛን ስኬት ማየት አይፈልጉም:: ከሰው በታች፣ ከሀገር ኋላ ቀርተን ለማኝና ተመጽዋች ሆነን፣ ሲጠሩን አቤት ሲልኩን ወዴት እያልን ታዛዥ ሆነንእንድንኖር ነው የሚፈልጉት:: በተመኘነው ልክ እንድናድግ፣ በምንፈልገው ልክ ቀና እንድንል የአንድነት ክንዳችን በፈጠሩት አባይ ላይም ሆነ በማንኛውም ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ልንተባበር ይገባል::

ጠላቶቻችንን የምናሳፍርበት ብቸኛው መንገድ አንድነት ነው:: ኢትዮጵያዊነት አስፈሪና ገናና የሚሆነው በአንድነት ውስጥ ብቻ ነው:: አባይ እንዴት ተገነባ? የአድዋ ድል እንዴት መጣ? ጣሊያንንና ግብጽን፣ እንግሊዝንና ሱማሊያ፣ ሌሎች ወደረኞቻችንን እንዴት ረታን ብለን ስንጠይቅ ስልጣኔ ሳይሆን፣ ዘመናዊነት ሳይሆን፣ እውቀትና ጥበብ ሳይሆን አንድነትን ነው የምናገኘው:: ማሸነፋችን ያለው አንድነታችን ውስጥ ነው::

አብዛኞቹ ታሪኮቻችን፣ አብዛኞቹ እሴቶቻችን በጋራ ሀሳብ፣ በጋራ እምነት፣ በጋራ ፍቅር እውን የሆኑ ናቸው:: በእድለኛና በባለድል ስም አባይን ጨርሰን ሌላ ግድብ፣ ሌላ ታሪክ እንድንሰራ የጽናት ክንዶቻችን ከአብሮነት አይቦዝኑ :: ለሀገር መልፋት ለራስ መልፋት ነው:: ይሄ ትውልድ ዝም ብሎ ባለድል አልሆነም..:: የገባው የሆነ ነገር አለ :: ሰው እውነት ሲገባው ለእውነት ብቻ ነው የሚለፋው:: ሰው ፍቅርና ፍትህ ሲገባው ለፍቅርና ለፍትህ ብቻ ነው የሚኖረው:: መለያየት ምን ያክል ክፉ እንደሆነ ይሄ ትውልድ ገብቶታል :: ከአባቶቹ የወረሰውን የመቻልና የማድረግ ወኔ አባይን እንዲገነባ መንገድ ከፍቶለታል:: ድህነት፣ ኋላ ቀርነት ክብረ ነክ እንደሆነ አውቆታል::

ልክ እንደ ህዳሴ ግድባችን አንዳንድ ታሪኮች ፍቅር ብቻ ነው የሚፈልጉት:: አባይ የመቶ ሀያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የፍቅር፣ የጽናት፣ የተስፋ፣ የህብረት ውጤት ነው:: የብዙ ድሀ ልቦች፣ የበርካታ ምስኪን ነፍሶች የደግነትና የመስጠት ሚስጢር ነው:: እንጂማ ምን ኖሮን፣ ምን ተርፎን አባይን የሚያክል ግዙፍ ፕሮጀክት እንገነባለን? አባይ የቆመው በፍቅር ነው:: አባይ የቆመው በህብረት ነው:: አባይ የቆመው በጽናት ነው::

# ሰውን ሰው ያደረገው ---

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በችግራችን ወቅት ስለሚደርስልን ብቻ ሳይሆን፤ ሰውን ሰው ያደረገው ዕቁብ ነው ስለተባለም ሳይሆን፤ የራሳችን አገር በቀል እውቀታችን ውጤት ስለሆነም ሳይሆን ...፤ ሁላችንም፣ እዚህም እዛም (ዲያስፖራ) ያለነው እንደምናውቀው እቁብ ከእኛው፤ ለእኛው፤ የእኛው .... የሆነ ማህበራዊ ተቋም ነው።

ምናልባት «የአካባቢ ፀበል ልጥ መንከሪያ ነው» እንደሚባለው ሆኖ እንደሆነም እንጃ ብዙውን ጊዜ ዕቁብ ሲባል እንደ ቀላል፤ እንደ ዋዛ የምንመለከት ቁጥራችን ብዙ ነው። ይህ ጸሐፊ እስከሚያውቀው ድረስ ለማህበራዊ ተቋማቶቻችን ልዩ ትኩረትን ሰጥተው የሠሩ አንድ ሰው ቢኖሩ ደራሲ፣ ተርጓሚና ጋዜጠኛ ማሞ ውድነህ ናቸው።

ማሞ ውድነህ እነዚህን አገር በቀል እውቀት አፈራሽ (ወይም አገርኛ) የሆኑ ተቋማትን ራሳቸውን አስችለው፤ በርእሰ ጉዳይነት አንስተው ለወግ ለማዕረግ አብቅተዋቸዋል። «እድርተኞቹ»፤ «ዕቁብተኞቹ»፤ «ማህበርተኞቹ» ሲሉም ተጠብበውባቸዋል። በእነዚሁ ሥራዎቻቸው አማካኝነትም የእነዚህኑ ተቋማት አስፈላጊነ ታቸውን፤አላማቸውን፤አተገባበርና ተግባሪያቸውን በዘመናዊ አስተሳሰብ የተረኳቸው ሲሆን፤ በተገቢው መንገድ አሽተውና ገርተው በእሴትነታቸው ይቆዩ ዘንድ አሳስበዋል። (እነዚህን «ልቦለድ» ሥራዎች፣ በተለይ ቀደም ያለው ትውልድ አሳምሮ ያውቃቸዋል ብለን በማሰብ ማሞን እያመሰገንን ማለፍን መርጠናል።) ወደ ባህር ማዶ እንዝለቅ።

ዕቁብ ሲያትል በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዘንድም ተጉዞ ከላይ ያልንለትን፣ «ሰውን ሰው ያደረገው ...» ብለን ያፀደቅንለትን ሥራ እየሠራ ይገኛል። ለጊዜው ሲያትልን እንጥቀስ እንጂ በሌሎቹ ዘንድ የለም እያልን አይደለም። «አበሻ ባለበት ሁሉ ...» እስኪባል ድረስ ሁሉም አለ።

በሲያትል እቁብተኞች ድረ-ገፅ ላይ ሰፍሮ እንደሚነበበው ዕቁብ የእንግሊዝኛ አቻው ወይም በፈረንጆቹ እይታ "Rotating Savings and Credit Association (ROSCA)" የሚል ብያኔ ተሰጥቶታል። ትክክል ነው። ምክንያቱ ደግሞ ዕቁብ ዙር መሆኑ፤ በዙር (እጣ) የሚደርስ መሆኑ፤ ሌላው የቁጠባ ዓይነት መሆኑና እንደየዕቁቡ ባህርይ (እንደየ ቤቱ) ብድር ወይም ቅድሚያ የሚሰጥበት ሁኔታ የመኖሩ ጉዳይ ነው።

ወደ ኢ-መደበኛ ፋይናንሳዊ ተቋምነቱ ዝርዝር ጉዳይ ከመሄዳችን በፊት የእቁብን ሌላ ገፅታ አስመልክተን አንድ ነገር እንበል።

ዕቁብ፣ ልክ እንደ እድር እና ማህበር ሁሉ ከዋና አላማው ባሻገር ሌሎች ተጓዳኝ አላማና ፋይዳዎችም አሉት። እነዚህ ፋይዳዎች በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊኖሩና ያ ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ይቀጥል ዘንድ እጅግ አስፈላጊ ከመሆናቸው አኳያ ዕቁብም ሆነ ማህበር እና እድር የሚጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም።

መቸም «እከሌ እኮ ዕቁብተኛዬ ነው፤ እከሌ እኮ ማህበርተኛዬ ነው፤ እከሌስ? እሱማ እድርተኛዬ ነው እኮ፤ አታውቅ(ቂ)ም እንዴ? ...» የመሳሰሉ አገላለፆችን የማናውቅ የለንም። እነዚህ አገላለፆች ደግሞ በማህፀናቸው ውስጥ የያዙት ማህበራዊ እሴት እንዲህ በቀላሉ ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም። መተማመን አለ፤ አንዱ ላንዱ ዋስ መኳኳን አለ፤ በመገናኘት ወቅት ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ አለ፤ ስለ ሥራ፤ ስለ አገር፣ ፖለቲካ፣ መንግሥትን ማማት (ያለ ምንም መፈራራትና ፍፁም መተማመን) .... ሁሉ አለ። ስለ ቤተሰብ፣ ትዳር፣ ልጆች .... ስለ ራስ፣ ጎረቤት፣ ጓደኛ ... ጤንነት ሁሉ መነጋገር አለ፤ አሳልፎ መሰጣጣት ሁሉ የለም። ይህ ደግሞ በመንግሥት የውይይት (ስብሰባም እንበለው) ደረጃ እንኳን የማይገኝ እሴት (ዲሞክራሲ) ነውና እድርም ሆነ፣ ማህበርና ዕቁብ ያላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በመሆኑም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

ወደ ተነሳንበት፤ ወደ ዕቁብ ኢ-መደበኛ ተቋምነት እንሂድ።

እቁብ ኢ-መደበኛ (በመንግሥታዊ አወቃቀርና መዋቅር ያልተደገፈ) ማህበራዊ የቢስነስ ተቋም ነው ብለናል:: ብዙዎች ዕድሜ ጠገብ ነው ቢሉትም፤ ከገንዘብ ሥሪት ጋር የተጣመረ በመሆኑ እንደ ዕድር ተቋማቶቻችን አንጋፋ አይመስልም::

በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሰፋ አድርገው የሄዱት የቺካጐ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን ዕቁብ በ1930ዎቹ በጉራጌ ሕዝብ አማካኝነት እንደተጀመረ ጽፈዋል:: የዲላ ዩኒቨርሲቲ የቢስዝነስና ምጣኔ ሀብት መምህር አዲሱ ካራፎ «በኮንሶ ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ማዕከላትን በመደገፍ ዕቁብ ያለው ሚና» (2017) በሚል ርእስ ባካሄዱት ጥናት፤ ዕቁብን አፍሪካ በቀል የፋይናንስ ተቋም መሆኑን ያስረዳሉ:: ዕቁብ በጋና ሱሱ፣ በናይጄሪያ ኢሱሱ፣ በማላዊ ቺፐረጋኒ፣ በታንዛኒያ ምቸዞ፣ እና በፈረንሳይኛ ተናጋሪ አፍሪካ አገሮች ደግሞ ቶንቲነርስ በመባል እንደሚታወቅም ያብራራሉ።

**የነጋዴዎች ዕቁብ በንግድ ቦታዎች በብዛት ዘወትር ከሰዓት በኋላ እየሰበሰቡ በተወሰኑ ቀናት የሚወጣበት ነው:: እንዲሁም በየዕለቱ ዕቁብ የሚሰበስቡ ግሮሰሪዎች ቡና ቤቶች አሉ፤ ይህም ከነጋዴዎች የሚሰበሰብና ዕጣ የሚወጣበት አሠራር ነው**

የደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላት ቃሉን ሲፈታው ዕቁብ የተጠበቀ፤ ጥብቅ፤ የመዋጮ ገንዘብ ባንድ ሰው እጅ ተጠብቆ በዕጣ ለዕቁብተኛው የሚታደል ይለዋል:: ቁብ የሚለው ቃልም ዐቀበ፤ዕቁብ ከሚለው ቃል ጋር ይመሳሰላል፤ ቁብ ፍቺው ዐሰበ፤ ግድ ይለዋል:: ቁብ የለሽ ሲልም ሀሳብ የለሽ፤ ግድ የለሽ ማለት መሆኑን ያስረዳል:: በግእዝ ዕቁብ የተጠበቀ፣ የተጠነቀቀ፣ ጥብቅ፣ ጥንቁቅ፣ የተቀመጠ፣ ያለ ማለት ነው:: በግእዝ ዕቀቡ ሕግየ ሲል ሕጌን ጠብቁ ማለት ነው:: (ዘሌ 19፡20) በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም አቁብ፤ ዕቁብ፣ አቃቢ፣ ጠበቀ፣ ከለከለ እንደማለት ነው በሚል ይፈታዋል:: መቆጠብ የሚለውም ቃልም ሲጠብቅ ገንዘብን ከማባከን መራቅ መጠንቀቅ ማለት ሲሆን፤ ሲላላ እየቀነሱ ማስቀመጥ ማለት መሆኑ ተፅፏል::

ፕሮፌሰር አየለ በከሬ የአፍሪካ አያዎ (Paradox) የሆነው ድህነት በአፍሪካ በቀል ዕውቀት፣ ባህላዊ ኩነቶችና በቀበሌያዊ ተቋማት ሚና እንደሚፈታ ይገልፃሉ:: ዕቁብ በጥቂት ሰዎች፣ በተዘዋዋሪ ብር አኗኗራቸውንና ሕይወታቸውን ለማሻሻል እንደሚቋቋም ጽፈዋል:: ይህም እንደ አባላቱ ፍላጎት በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ነው፤ እንደ ዕድር ግን ዘለቄታዊ ዕድሜ የለውም ይላሉ::

ዕቁብ ብዙውን ጊዜ የሚሰበሰበው በአንድ አካባቢ በሚኖሩ፣ በሚሠሩ በሚተዋወቁ እና በሚተማመኑ፤ እንዲሁም በብዛት ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ባላቸው ሰዎች ነው:: የዘመናችን ዲጂታል ዕቁብ ግን በየትኛውም ቦታ ያሉ ሰዎች ገንዘብ እንዲጥሉ እያደረገ ነው። (100ሺህ ሰዎች ዕቁብ የሚጥሉበት «በ30 ወራት የሚያልቅ» የሚል መረጃ አይቻለሁ።) በኪስ ስልክና በመረጃ መረብ የሚታገዝ፤ የዲጂታል ዕቁብ አስተማማኝነቱስ? የሚለውን ግን ከስልጣኔ፣ ዝማኔና እምነት ጋር የሚያያዝ ስለሆነ እዚህ አስፍተን የምናየው ሳይሆን ጊዜ የሚመልሰው ይሆናል (በተለይ የእኛን በመሳሰሉ አገራት)።

ሰዎች የገንዘብ እጥረት በሚያጋጥማቸው ጊዜ ዕቁብን እንደ አንድ መውጫ መንገድ ይጠቀሙበታል:: የዕቁብ ተጠቃሚዎች፣ ሌኒን እንዳይሰማቸው እንጂ፣ «ሰውን ሰው ያደረገው ዕቁብ ነው» ሲሉ ይሰማል:: በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓ እና በአረብ ሀገራት፤ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጭምር ዕቁብ እየሰበሰቡ ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን እንደሚፈቱ እራሳቸው ሲናገሩ ይሰማሉ:: በደርግ ውድቀት ከሀገር የወጡት ፈላሻዎችም በእሥራኤል ዕቁብን እንደችግር መፍቻ አማራጭ ይጠቀሙበታል:: ጌታቸው መኳንንት የኢመደበኛ ተቋማት (ዕቁብ፣ ዕድርና ማኅበራት) ሚና የስደተኛ ዜጎችን ሕይወት በማስተካከል፤ በሚል ባቀረቡት ጥናት በካናዳ ቶሮንቶ ኢትዮጵያውያን ዕቁብ እየሰበሰቡ ችግሮቻቸውን ይቀርፋሉ፤ መኖሪያ ቤት፣ ተሽከርካሪ .... የመሳሰሉትን በመግዛት፤ የተሻሉ ሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ራሳቸውን ያጠናክራሉ ይላሉ::

በጋራ ዕቃ ለመግዛት የሚጠቀሙበትም አሉ:: መጽሐፍ የሚገዙ (የመጽሐፍ ዕቁብ)፤ ቴሌቪዥን፣ ማቀዝቀዣ ወይም ሶፋ ከአንድ ንግድ ቦታ ለመግዛት ዕቁብ የሚጥሉ አሉ:: ሰብሳቢው አስቀድመው ዕቃውን ከሚገዙት ድርጅት ተስማምተው ዕጣ ለወጣለት እየሄደ ከንግድ ቦታው ዕቃውን እንዲወስድ ያደርጋሉ:: ገንዘቡን ቢፈልግ አይሰጠውም:: የተስማማው ዕቃውን ለመግዛት ስለሆነ ማለት ነው:: ሰብሳቢው በቀዳሚው ዕጣ ዕቃውን ወይም ብሩን ሲወስድ፤ ከንግዱ ተቋሙ ደግሞ የተወሰነ ጥቅም እንደ ውለታ ይሰጠዋል::

የዕቁብን የአባላቱ ብዛት ገንዘቡ የሚሰበስብበት ቦታ እና ጊዜ፣ መጠን፣ በምን ያህል ጊዜ እንደሚወጣ የሚወሰነው በሰብሳቢው ነው:: አንዳንዴ ሰብሳቢውና ተሰብሳቢው ሊወስኑ ይችላሉ::

በብዙ ቦታዎች በዕቁብ አሰባሰብ፣ አሠራርና ውስጣዊ ደንብ መሠረት ዳኛውና ሰብሳቢው የመጀመሪያውን ዕጣ መውሰዳቸው የተለመደ ነው:: የመጀመሪያው የዳኛው፤ ሁለተኛውን ደግሞ የሰብሳቢው።

የዕቁብ አባላት፣ እቁብተኞች (በተለይ አንድ ቤተሰብ ከሆኑ) ገንዘቡን ለጋራ ዕድገት ይሠሩበታል:: አንዳንዴ ዳኛውም ሰብሳቢውም አንድ ሰው ይሆንና ቀዳሚውን ዕጣ በመውሰድ ለቀጣዮቹ በየጊዜው ዕጣ እያወጣ ወይም አንዴ ሁሉንም አውጥቶ በየጊዜው በተራ ይሰጣል:: ዕቁቡን በልቶ ቀጣዩን ለመጣል ደግሞ የሚያስቸግር የሚያስቀርም ካላ ጣጣው የዳኛው ይሆናል:: ቅድሚያ ይበላ ዘንድም ውስጠ ደንቡ ከሚፈቅድባቸው ምክንያቶች አንዱም ይሄው ነው።

እንደምናውቀው በኢትዮጵያ ብር ከብድር ተቋማት ማግኘቱ እንዲህ ቀላል አይደለም፤ ሲበዛ ውስብስብ ነው። ተገኘ ቢባል እንኳን ለተደቀነ ችግር አፋጣኝ መፍቻ አይሆንም፤ አይደርስም። ባንኮች ገንዘብ በመጠበቅና በማስቀመጥ ሁሉን ቢያስተናግዱም በማበደር ረገድ ድሃውን ዘንግተውታል:: ዜጋው ግን ዕቁብን በመሰብሰብ ችግሩን ይፈታል:: የሚፈልገውን ያሟላል:: ለኅብረተሰብ ቁልፍ ችግር መፍቻው አገር በቀል እውቀት ሆነ ማለት ነው፤ ሀገርኛ ማለትም ይሄው ነው።

በብዛት በልምድ የሚካሄደው ዕቁብ፤ ገንዘቡ ከፍ ያለ ከሆነ ተዘጋጅቶ በአባላቱ በፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ ይመራል:: የዕቁብ መተዳደሪያ ሕግና ደንብ የሚተላለፉ ይቀጡበታል:: ዎልፍ ሌስላውና ቶማስ ኤል.ካኔ ባወጡት አንድ መጽሐፍ የነጋዴዎች፣ የመንደርተኞችን ጨምሮ የሠራተኞች፤ ማለትም የተቀጣሪዎችና የደመዝተኞች የተባሉ የዕቁብ ዓይነቶች እንዳሉ ይገልፃሉ::

የነጋዴዎች ዕቁብ በንግድ ቦታዎች በብዛት ዘወትር ከሰዓት በኋላ እየሰበሰቡ በተወሰኑ ቀናት የሚወጣበት ነው:: እንዲሁም በየዕለቱ ዕቁብ የሚሰበስቡ ግሮሰሪዎች ቡና ቤቶች አሉ፤ ይህም ከነጋዴዎች የሚሰበሰብና ዕጣ የሚወጣበት አሠራር ነው:: የደረሰው ዕጣ ቁጥሩ በአነስተኛ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ተጽፎ መጠጥ ቤቶች ግድግዳ ላይ ሲሰቀል አሁንም ይታያል:: የሠፈር ዕቁብ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በሳምንት ገንዘብ ሰብስበው ዕጣ የሚያወጡበት ነው:: በተለይ በመንደር ዕቁብተኞች፤ ወይዛዝርት ከሆኑ ቡና አፍልተው የቡና ቁርስ ቀማምሰው ተጨዋውተው ዕጣውን አውጥተው ይለያያሉ::

ጎልማሶች ከሆኑም ዕቁባቸውን ሰብስበው ዕጣ አውጥተው፤ ቢራ፣ ለስላሳ ጠጥተው ሳምንት ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ:: ለዚህ ነው ሰዎች ሲናገሩ ከእነርሱ ጋር እኮ ዕቁብ እጠጣለሁ የሚሉት:: ዕጣ የሚደርሰውም የ«ፍንጥር» ብሎ አባላቱን የሚጋብዝ አለ። ይህም ተገዶ ሳይሆን ወዶ፣ በፍቅር የሚያደርገው ነው:: በእንደዚህ ዓይነት ዕቁብ ዕጣው ሲወጣ፣ ዕጣው የደረሰው ባለ ዕጣ ገንዘብ በአስቸኳይ እፈልጋለሁ፣ ቸግሮኛል የሚል አባል (ዕቁብተኛ) ካለ ዕጣውን በተወሰነ ገንዘብ ይሸጥለታል:: ዕጣውን ያሳለፈው ዕቁብተኛ ደግሞ የሸጠለትን ሰው ዕጣ ጠብቆ በደረሰው ጊዜ ይወስዳል:: በደሞዝተኞች (ቢሮዎች አካባቢ) ገንዘብ የቸገረው ካለ ዕጣውን ከሚወስደው ሰው ጋር በመነጋገርና በመመካከር ነው የሚያልቀው። ሁለቱ ብቻ የሚጨርሱት ይሆናል።

ሁሉም ደርሶት ሲጠናቀቅ አንዳንድ ዕቁቦች፤ በግ ወይም በሬ አርደው ጠጅ፣ ቢራ አወራርደው፤ ለቀጣይ ያገናኘን ብለው ያሰነባበታሉ:: ይህም ከፊሎቹ ከየዕቁብተኛው በትርፍ መዋጮ እየተሰበሰበ ሲጠናቀቅ የሚደረግ ነው:: ዳኛው በፈቃዱ የሚያደርገውም ግብዣ አለ:: (ይህ ሁሉ፣ እያንዳንዱ ተግባር እራሱን የቻለ ማህበራዊ እሴት መሆኑን ልብ ማለት ያሻል።)

ትልልቅ ዕቁብ ሲሆን ጠበቃ ያዘጋጃሉ:: ባለ ዕጣው ተያዥ ማምጣቱ ግድ ይሆናል:: ከአባላቱ ሁለት ሦስት ዋስ ማለት ነው:: ዕቁብ የበላው ቀጣይ ክፍያ ቢያቋርጥ ዋስ የሆነለት ሰውዬ ዕጣው ሲደርሰው ገንዘቡ ይያዝበታል::

በመንግሥት ሠራተኞች ያለው ዕቁብ አሰባበሰብ በየወራቱ ሆኖ ብዙ ጊዜ መንፈቅና ዓመት የሚቆይ ነው:: ሰብሳቢው የመጀመሪያውን ዕቁብ ወስዶ ገንዘቡን በተራው በየወሩ ይጥላል:: ከንግድ ቦታዎች የሚለየው ሰብሳቢው የመጀመሪያውን ዕጣ መውሰዱ ብቻ ነው:: ቀሪዎቹን ጊዜያት እሱም ከዕቁብ አባላቱ ዕኩል ገንዘብ በየወሩ ይጥላል:: ሰብሳቢው ዕቁብ ከሚጥሉት መካከል አንዱ ቢከደው (ብዙ ጊዜ አይከሰትም) ወይም ዕቁብ መጣሉን ቢያቆም አግባብቶ እንዲጥል ማድረግ አልያም ዕዳውን ሰብሳቢው መወጣት ይጠበቅበታል::

ሌላው የዕቁብ ፀጋ ዕቁብተኛ ለመሆን ዖታ፣ ጎሳና እምነት የሚጠይቅ አለመሆኑ ነው:: ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው። የአባላቱ የኑሮ ደረጃ መመጣጠን ግን ግድ ነው፤ ዋናው የሚጣለውን የዕቁብ መዋጮ ይችለዋል ወይ? የሚለው ጉዳይ መሠረታዊ ነው ማለት ነው::

በአጠቃላይ፣ ወንዝ አፈራሽ የሆነው ዕቁብ ጥሪት ለመሰብሰብ፣ ችግርን ለመቅረፍ፣ እንዳስፈላጊነቱ ደረጃ በደረጃ የቤት ቁሳቁስ ለማሟላት፣ ሦስት ጉልቻ ለመመሥረት፤ ቤት ለመሥራት በነጋዴዎች ደግሞ የንግድ ደረጃቸውንና ዐቅማቸውን ለማሻሻል (ለአራት ዓመት ከ30 ነጋዴዎች ዕቁብ እሰበስብለት የነበረ ግለሰብ፤ ሁለት ተሽከርካሪዎች መግዛቱን ስመለከት ዕቁብ ፋይዳ ያለው መሆኑን በውል ተገንዝቤያለሁ) ወ.ዘ.ተ የሚረዳ ኢ-መደበኛ የገንዘብ ተቋም ነው:: ማኅበራዊ ሕይወትን ለመጋራት (ሳይቸግረው ዕቁብ የሚሰበስበውን ሰው ለማበረታታት) ለፍጆታ፣ ለኢንቨስትመንት፣ ወዳጅ ዘመድን ለመርዳት፣ አስቸኳይ የገንዘብ ፍላጎትን ለማሟላት ይረዳል:: አንዳንዶችም ገንዘባቸውን ከብክነት ቆጥበው የተሻለ ነገር ያደርጉበት ዘንድ ያነሳሳቸዋል:: በመሆኑም፣ ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ ነውና «እቁብ ለዘላለም ይኑር!!!» እንላለን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች




ጉባኤው የወጣት አመራሮችን ብቃት ለመገንባት የሚያስችል ግብአት ተገኝቶበታል፤

## የወጣት አመራሮችን ብቃት ለማዳበር

አስናቀ ፀጋዬ

ሁለተኛው የ 2022 የወጣቶች አመራር ጉባኤና ውድድር «ድምፄ ለግድቤ» በሚል መሪ ቃል ሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ በተሰኘ ድርጅት አዘጋጅነት ከኢፌዴሪ ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለሶስት ተከታታይ ቀናት አካሂዷል።

የወጣቶች አመራር ጉባኤና ውድድር ዋና አላማ እየመጡ ያሉ አዳዲስ ወጣት አመራሮችን በህዝብ ፊት ንግግር ክህሎት፣ በድርድር፣ ዲፕሎማሲና የፖለቲካ አስተሳሰብ ብቃት ማገዝ ነው። የዘንድሮው ደግሞ የወጣቶችን የአመራር ክህሎት በቀጠናዊ፣ በአህጉራዊና በአለም አቀፍ ደረጃ ለማዳበር ታስቦ ተዘጋጅቷል።

በሴፍ ላይት ኢንሼቲቭ የአለም አቀፍ ግንኙነት ሃላፊ አምባሳደር ምህረት ህሩይ እንደሚያብራሩት ሴፍ ላይት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን እ.ኤ.አ ከ2018 ጀምሮ በወጣቶች ላይ ሲሰራ ቆይቷል። በተለይ ደግሞ አዳዲስ እየመጡ ያሉ ወጣት ዲፕሎማቶችን ማውጣት ላይ ስራዎችን ይሰራል። እስካሁንም በርካታ ወጣቶችን አሰልጥኗል። ለዚህም «3 H» የተሰኘ አካሄድ ይከተላል።

ይህም ጭንቅላት/Head/ ወይም ደግሞ አመለካከት ላይ ወጣቶች በአእምሮ የዳበረና እውቀት ያለው የአመራር ጥበብን እንዲላበሱ ስልጠናዎች እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ልብ /Heart/ ላይ ወጣቱ አስተሳሰቡ ተቀይሮ በልቡም እንዲቀየር ባህሪ የመገንባት ስራዎች ይሰራል። ለአብነትም ወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶችን እንዲሰጡና ከልብ የመነጨና ትክክለኛ ባህርይ ብሎም የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያሳዩ ይደረጋል። እጅ /Hand/ በተሰኘው አካሄድ ደግሞ ድርጅቱ በአእምሮና በልባቸው የተቀየሩ ወጣቶች እጃቸው እንዲዘረጋና እንዲሰራ ወይም ድጋፍ እንዲያደርግ ስራ ፈጠራና ክህሎት ላይ ይሰራል። ዲፕሎማሲና ትምህርት ላይም ተመሳሳይ ስራዎች ይሰራሉ።

እንደ ሃላፊዋ ገለፃ የወጣቶች አመራር ኮንፍረንስና ውድድር አምና የተጀመረ ሲሆን ሀገርኛና ሀገርን በሚያስተዋውቁ ስራዎች ላይ በይበልጥ ያተኮረ ነበር። በዚህ የመጀመሪያ ኮንፍረንስ ወጣቱ ሀገሩን ማስተዋወቅ እንዲለማመድ ታሳቢ በማድረግ ከ120 በላይ ወጣቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል። በዚህ ኮንፍረንስም በሁሉም የአዲስ አበባ ከተማ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ ወጣቶች ተመርጠው እንዲካፈሉ ሆኗል።

ወጣቶቹ በጤና፣ ትምህርት፣ የህዝብ አገልግሎትና ቢዝነስ ዘርፎች ገብተው እንዲወዳደሩና የተሻሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን በየሴክተሩ እንዲያመጡ ከተደረገ በኋላ በሁለተኛው የወጣቶች አመራር ኮንፍረንስና ውድድር በአንክሮ ማሰብ፣ በህዝብ ፊት የመናገር ክህሎት፣ በዲፕሎማሲ ሰላማዊ ንግግርና አመራርን እንዲለማመዱ መድረኩ ተዘጋጅቷል። ይህም የሚሆነው ወጣቶቹ በቅድሚያ ከወራት በፊት ምዝገባ አካሂደው ከሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ ጋር እንዲሰሩና እንዲያጠኑ ከተደረገ በኋላ ነው።

ይህንኑ መሰረት በማድረግ «ድምፄ ለግድቤ» በሚል መሪ ቃል በተለይ ወጣቶች የአፍሪካን መፍትሄ በአፍሪካ ወጣቶች እንዲሆን በማሰብ አፍሪካ ህብረትን በአንደኛው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀጥታውን ደግሞ በሁለተኛው ኮሚቴ ውስጥ በማድረግ ሁለተኛው የወጣቶች አመራር ኮንፍረንስና ውድድር በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

የአባይ ጉዳይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ድረስ ሄዶ ስለነበር ወጣቶቹ በዚህ ምክር ቤት የታላቁ ህዳሴ ግድብን በሚመለከት ሀሳባቸውን ለማንጸባረቅ እንዲያስችላቸው በኮሚቴው ውስጥ ልምምድ ያደርጋሉ።

በአፍሪካ ህብረት ኮሚቴ ውስጥ ያሉት ደግሞ የአፍሪካ ሀገራትን ወክለው ሃሳባቸውን ያቀርባሉ። አፍሪካውያን ወጣቶች ሀገራቸውን ወክለው በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዙሪያ ጥናት አድርገው ፅሁፍ እንዲያስገቡ ከተደረገ በኋላ በኮንፍረንሱ ላይ ክርክር እያካሄዱ ለታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ የመፍትሄ ሀሳብ አቅርበዋል። ሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ ደግሞ ይህን የመፍትሄ ሀሳብ በአንድ ጨምቆ ለሚመለከተው አካል ሰጥቷል።

ከዚህ በፊት የተካሄደው የወጣቶች አመራር ኮንፍረንስና ውድድር ወጣቶች የአመራር ብቃት ማደግ ላይ የራሱን አስተዋፅኦ በማድረጉ በርካታ ወጣቶች ከሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ ጋር በጋራ እየሰሩ ይገኛሉ። አብዛኛዎቹ ደግሞ ገና በትምህርት ገበታቸው ላይ እያሉ በተለያዩ የአመራርነት ቦታዎች ላይ ገብተው መስራት ችለዋል። በውስጣቸው ያለውን እምቅ የአመራርነት ክህሎት እንዲያወጡም አስችሏቸዋል።

ይህ ኮንፍረንስ የሚዘጋጀው ወጣቶች የአመራር ብቃታቸውን አስቀድመው እንዲያዳብሩ ለማስቻል ብቻ ሳይሆኑ ብቃቱ ያላቸውን ወጣቶችን ለመሰብሰብ በመሆኑ በሴፍ ላይን ኢኒሺዬቲቭ ውስጥም ሆነ በሌሎች ተቋማት ገብተው በአመራርነት እየሰሩ የሚገኙ ወጣቶች አሉ። ፕሮግራሙ ሲዘጋጅ በማስተባበር ሲሰሩ የቆዩ ወጣቶችም ነበሩ።

ባለፈው ዓመት ኮንፍረንስ ላይ የነበሩ ወጣቶችንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ለትምህርት ቤት አምባሰደር በማድረግ ይህንኑ እንዲለማመዱ እየተደረገ ይገኛል። በቀጣይም በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ሁሉም የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ሞዴል የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ማቋቋምና ይህንንም ደግሞ በየትምህርት ቤቶቹ ላይ ራሳቸው ተማሪዎች እንዲተገብሩት ይደረጋል።

ለአብነትም ወጣቶቹ በሴፍ ላይት ኢኒሼዬቲቭና በትምህርት ቤቶች መካከል ድልድይ ሆነው እየሰሩ ይገኛሉ። መምህራንና ርእሰ መምህራንን አማክረው የጋራ መግባቢያ ስምምነት አስፈርመው ክለብ ያቋቋሙ ወጣቶችም አሉ።

ሃላፊዋ እንደሚገልፁት በዚህ የአመራር ጉባኤና ውድድር የሚሳተፉ ወጣቶች እድሜያቸው ከ24 እስከ 30 ያሉ ቢሆንም አንዳንዴ እስከ 35 ዓመት ያሉም እንዲሳተፉ ይደረጋል ። ወጣቶቹ በጉባኤው እንዲሳተፉ የሚደረገው አንድም በእንዲህ ዓይነቱ መድረክ ላይ የሚሳተፉትን ለመመልመል በሌላ በኩልም ማንኛውም በአመራር ጉባኤና ውድድር ላይ መሳተፍና በዲፕሎማሲ ላይ መስራት የሚፈልግ ወጣት ሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ ጋር ሄዶ በመመዝገብ ነው። ለዚህም ድርጅቱ ዩኒቨርሲቲዎች ድረስ በመሄድ ወጣቶች በአመራርና በዲፕሎማሲ ጉባኤ ላይ እንዲሳተፉ እያደረገ እግረመንገዱንም ራእዩን እያስተዋወቀ ይገኛል።

ወጣቱ የሀገሪቷ እምቅ ሃብት ያለው በመሆኑ በቅድሚያ ትምህርት በመስጠት፣ በየትምህርት ቤቶች በመሄድና የድርጅቱን ራእይ በማስተዋወቅ ወጣቶቹ እንዲቀላቀሉ ይደረጋል። ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ደግሞ ተመዝግበው እንዲህ ዓይነቱን ኮንፍረንስ እንዲሳተፉ ይደረጋል።

በቀጣይም እንደ ሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ ድርጅቱን ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ወጣቶችንና የተለያዩ ሀገራት ወጣቶች መካከል ድልድይ ሆኖ የመስራት ፍላጎት አለ። በተለያዩ ሀገራት ያሉ ወጣቶችን ወደ ኢትዮጵያ ማምጣትና ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ የሀገሪቷን በጎ ገፅታ የመገንባት ስራ ይከናወናል።

በሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ በትንሹ የተጀመረው ስራ አሁን አድጎ ከፌዴራል ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚንስቴር ጋር በመተባበር እየሰራ ነው። ሁሉንም ክልሎች ያካተተ ነው። በቀጣይ ደግሞ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል።

በሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ የኮሚዩኒኬሽን ሃላፊ አቶ ስምኦን ጌትነት እንደሚናገሩት ድርጅቱ በቅድሚያ ወጣቶች ቀና እንዲያስቡ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ ልምድም ያካፍላል። በመቀጠል ደግሞ በወጣቶች እችላለሁ ወይም አደርጋለሁ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ እንዲይዙ በአስተሳሰብ ለውጥ ላይ ይሰራል። በኋላ ላይ ደግሞ ወጣቶች የተለያዩ ክህሎቶችን ለማዳበር በሚያስችሏቸው ጉዳዮች ላይ ይሰራል።

ድርጅቱ እነዚህን ስራዎች ሲሰራ የሶስት፣ አስርና የሰላሳ ዓመት እቅዶችን ይዞ ሲሆን በአሁኑ ግዜ ግን በአብዛኛው ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ ያለው አመራርነት ላይ ነው። በመቀጠልም ወጣቶች የስራ ቅጥር ላይ እንዳይቸገሩና በስራ ቅጥር ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ስራዎችን ይሰራል።

ወጣቶች ወደ ስራው አለም ለመቀላቀል የሚያስችሉ መንገዶችንም ድርጅቱ ያመላክታል። አዳዲስ ተመራቂ ወጣቶች ያላቸውን ብቃት ተረድተው በየትኛው መስክ ላይ መስራት እንደሚችሉና ራን መግለጫ (ሲቪ) እንዲፅፉ ያግዛል። ከወጣቶች ጋር አንድ ላይ ለመስራት የሚያስችሉ ስልጠናዎችም ይሰጣሉ።

ለአብነትም የእንጨት ስራ ስልጠናን መጠቀስ ይቻላል። የራሳቸውን ቢዝነስ እንዲጀምሩም የስራ ፈጠራ ስልጠናዎችንም ይሰጣል። በተመሳሳይ ዲጂታል ትምህርት ላይም ድርጅቱ ለወጣቶች ስልጠና ይሰጣል።

ወጣቶች እነዚህ ስልጠናዎችና የክህሎት ትምህርት የሚያገኙት በድርጅቱ ማህበራዊ ድረገፅ http://www.safelightet.org/ እና የፌስቡክ አድራሻ ላይ የሚወጡ መረጃዎችን በማየትና በአካል የድርጅቱ ቢሮ በመሄድ በመመዝገብ ነው።

ድርጅቱ ለትርፍ ያለተቋቋመ ቢሆንም ትርፍ ላልሆነ ፕሮጀክቱ ፈንድ መጠየቅ እንጂ በራሱ ማሰባሰብ የማይችል በመሆኑና በዚህም እየተቸገረ በመሆኑ መንግስት ሲፈቅድ በቀጣይ ወደ ትርፍ መስራቱ የሚገባ ይሆናል።

የኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ እንደሚገልፁት የኢትዮጵያ ወጣቶች ፖሊሲ ወጣቱ አገራዊ አንድነት እንዲያመጣ፣ የክፍለ አህጉራዊ፣ አህጉራዊና አለም አቀፍ ግንኙነትና አጋርነትን በመፍጠር የወጣቶች ሁለንተናዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ በትብብር እና በመተሳሰብ ለወጣቶች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዲቻል ተደርጎ ተቀርጿል።

መንግስትም ወጣቶችን በሰላም ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ የሰላም አምባሳደሮች እና ዲፕሎማቶች ሆነው ለቀጠናዊ፣ ለሀገር አቀፍ እና ለአለም አቀፍ ሰላም፣ ልማት እና ብልፅግና አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።

በሴፍ ላይት ኢኒሺዬቲቭ የተጀመረው የወጣቶች የአመራር ኮንፍረንስና ውድድርም ወጣቶች ራሳቸውን ለተለያዩ ፈተናዎችና ድሎች እንዲያዘጋጁ ፣ ራሳቸውን እንዲያበረታቱ ፣ እንዲወዳደሩ ፣የሌላውን አመለካከት እንዲያከብሩና የመሪነትን ባህሪን እንዲያዳብሩ የሚያስችል በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው።

የኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ ክብርት ሙና አህመድ በበኩላቸው እንደሚሉት የወጣቶች የአመራር ክህሎት ውድድርና ኮንፈረንስ የኢትዮጵያን የወደፊት መሪዎች በአለም አቀፍ እና አህጉራዊ መድረክ ላይ በእውቀትና በበሳል የአመራር ጥበብ እንዲያድጉ መሰረት ይጥላል ።

ኮንፈረንሱ ወጣት መሪዎች ወደፊት የሀገርን ጥቅም ለማስከበርና ሀሳባቸውን በአለም አቀፍ ደረጃ በነፃነት እንዲገልጹ ያስችላቸዋል። በተለይም ኮንፍረንሱ ወጣቶች በአመራር ረገድ ያላቸውን እውቀት እንዲያዳብሩና በቀጣይ ለሚኖራቸው ሃላፊነት አገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ወዳጅነትን ለመፍጠርና ብሄራዊ ጥቅምን ለማስከበር የላቀ ሚና ይኖረዋል።

# የምድር በረከት

## የተፈጥሮ ጋዝ ጥናት ውጤቱ የምስራች

**ስምስም መንግሥቱ**

ያለማንም ከልካይ ከከርሰምድር ውስጥ ፈንቅሎ በመውጣት ሜዳውን አቋርጦ ወንዝ ውስጥ ይቀላቀላል:: የአካባቢው ነዋሪ ለላምባ ይጠቀምበት እንደሆን እንጂ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከት እየቻለ ሀብቱ እንደወራጅ ውሃ ሲወርድ እንደዋዛ እየታየ አመታት ተቆጥረዋል::በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን ውስጥ ለገሂዳና ወረኢሉ ወረዳዎች ድንበር ላይ መቸላ ወንዝ አቅራቢያ ስለሚገኘው የተፈጥሮ ጋዝ ነው የምናወራው:: ሀብቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዲኖረው በደቡብ ወሎ ዞን በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ሥር የሚገኘው የማዕድን ዘርፍና በጥናትና ምርምር ከተሳተፈው ወሎ ዩኒቨርሲቲ ከጥቂት ወራት በፊት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ሀብቱ ስለመኖሩ እንጂ ትክክለኛው ጊዜ አይታወቅም:: መኖሩ የተረጋገጠውም በአካባቢው አርሶአደሮች ጥቆማ ነው::

ይሁን እንጂ በ2000 ዓ.ም ትኩረት አግኝቶ እንቅስቃሴ ተደርጓል:: ሳልኮም ፔትሮሊየም የተባለ ኩባንያ በ2005 ዓ.ም ከማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ አግኝቶ በአካባቢው ላይ የጥናት ሥራ ለማካሄድ እንቅስቃሴ ጀምሮ ነበር:: ኩባንያው ይህ ነው የሚባል ሥራ ሳይሠራ አካባቢውን ጥሎ መውጣቱን በዞኑ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ የማዕድን ዘርፍ ቡድን መሪ አቶ ጀማል እድሪስ ይገልጻሉ::

በወሎ ዩኒቨርሲቲ የጂኦሎጂ ትምህርት ክፍል በኢንጂነሪንግ ጂኦሎጂ የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ዶክተር ደሳለኝ ገዛኸኝ እንደተናገሩት፤ ወሎ ዩኒቨርሲቲ 2011 ዓ.ም የጥናት ቡድን በማቋቋም ጥናቱን አካሂዷል:: የጥናት ቡድኑም በስፍራው ተገኝቶ ያረጋገጠው ከመሬት እየወጣ የሚፈስ ነዳጅ መኖሩን ነው:: የመንደድ ባህሪ ማሳየቱም ነዳጅ ስለመሆኑ አንዱ ማረጋገጫም ስለነበር በዚህ መንገድም ተፈትሾ ተረጋግጧል:: የጥናት ቡድኑ ናሙና ይዞ ወደ ዩኒቨርሲቲው በመመለስ በቤተሙከራ ውስጥ በተከናወነው የምርምር ሥራ ከፍተኛ የሆነ (98 በመቶ) የነዳጅ ድፍድፍ መኖሩ ነው የተረጋገጠው::

ዩኒቨርሲቲውም ሀብቱ ስለመኖሩ ከማረጋገጥ በላይ ብዙ ርቀት አልሄደም:: በወሎ አካባቢ በጥናት የተደገፈ በከርሰ ምድር ውስጥ የተፈጥሮ ነዳጅ ስለመኖሩ ለአብነት አነሳን እንጂ ኢትዮጵያ ከኦጋዴን እስከ ኦሞ፣ ከኦሞ እስከ ጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብና ምሥራቅ አካባቢዎች የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ዘይት ሀብት ክምችት ባለቤት ስለመሆኗ በተለያዩ ጊዜያት ሲገለጽ ቆይቷል:: በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ነዳጅ ፍለጋ ሥራ የተጀመረው እኤአ በ1950ዎቹ ሲሆን፣ ፍለጋውም በምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴን አካባቢ የተካሄደ መሆኑን ማዕድን ሚኒስቴር፤ የተፈጥሮ ጋዝ ምንነትና በኢትዮጵያ ያለበት ደረጃ በሚል በድረገጹ ያስነበበው መረጃ ያስረዳል:: አገሪቱም በነዳጅ ፍለጋ ለተሰማሩ ኩባንያዎች ፈቃድ በመስጠት የፍለጋውን ሥራ ስታከናውን ቆይታለች:: በተለይም እ.እ.አ ከ2003 ጀምሮ በተለያየ ሁኔታ የዓለምአቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በነዳጅ ፍለጋ ሥራ ተሰማርተዋል:: ማዕድን ሚኒስቴርም ከነዚህ ኩባንያዎች ጋር እስከ 25 አመት የሚቆይ የነዳጅ ምርት ሽርክና ስምምነት፣ ከሁለት አመት ያልበለጠ የጥምር ጥናት ስምምነት፣ በሚሉ የስምምነት ዓይነቶች በመፈራረም ሲሠራ ቆይቷል:: በዚሁ መሠረትም 16 የስምምነት ሰነዶች ተፈርመዋል:: ባለፉት 10 አመታትም ሰፋ ያለ የጥናት ሥራ ተሠርቷል:: በጥናት ሥራውም ኦጋዴን ውስጥ በካሉብ፣ በሂላላ እና በገናሌ አካባቢዎች ወደ 4ነጥብ7 ትሪሊዮን ኪዩቢክ ፊት የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት መኖሩ መረጋገጡን የሚኒስቴሩ የቆየ መረጃ ያመለክታል::

በኢትዮጵያ ያለውን የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት እና የነዳጅ ፍለጋ ሥራ ለማጠናከርና ወደ ምርት ለማስገባት እንዲያስችል የነዳጅ ሥራዎች ፖሊሲና አዋጅ መውጣቱም ይታወሳል::በፖሊሲው ከተካተቱት ዓላማዎች መካከል በክልልና በፌዴራል መንግሥት መካከል የተቀናጀ አሠራር ለመዘርጋት፣ ከዘርፉ ጋር በተያያዘ የአገር ውስጥና የቀጠናውን የገበያ ዕድል በመዳሰስ የተሻለ የገበያ አማራጭ ለመፈለግና ተወዳዳሪ የሆነ ሥርዓት መዘርጋት የሚሉት ይጠቀሳሉ:: እነዚህ ሁሉ የመንግሥት ጥረቶች በሀብቱ ለመጠቀም የተከናወኑ ተግባራትን ያሳያሉ:: መንግሥት ቢለዋወጥም ከሀብቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚደረገው ጥረት እንደቀጠለ ነው:: በማዕድን ልማት የሚታወቁ




የውጭ ኩባንያዎችን ወደ አገር በማስመጣት የፍለጋና የአዋጭነት ጥናት እንዲያካሂዱና ወደ ልማቱም እንዲገቡ እንዲሁም ዘርፉ ላይ የነበሩ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችል የፖሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ ጭምር ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ይገኛል::

የነዳጅ ሀብት ፖለቲካዊ አንደምታም ያለው በመሆኑ ከሀብቱ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ:: ኢትዮጵያ በተፈጥሮ የታደለችውን የከርሰ ምድር ሀብቷን ለኢኮኖሚ ጥቅም እንዳታውል ፀጥታ በማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች የሚያደርሱት ተጽእኖ ሌላው ተግዳሮት ነው:: በሶማሌ ክልል በደገሃቡር ዞን አቡሌ በተባለ ቦታ በነዳጅ ፍለጋ ላይ ተሰማርተው እያሉ በፀረሰላም ኃይሎች 65 ኢትዮጵያውያንና ዘጠኝ ቻይናውያን ሕይወታቸውን ያጡበትን ጊዜ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም እትሙ ያስታውሰናል::

አሁንም በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋለው የፀጥታ መደፍረስ የማዕድን ዘርፉን እየፈተነው ይገኛል:: የፀጥታ ችግር የተለያዩ ኩባንያዎችና የማዕድን አካባቢዎች ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ማድረጉን ማዕድን ሚኒስቴር መግለጹ ይታወሳል:: ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር የፀጥታ ስጋቱን ለመፍታት የበኩሉን ጥረት እያደረገ መሆኑንም ነው ያስታወቀው:: በክትትልና ቁጥጥር ቁርጠኛ ሆኖ መሥራት ላይ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ሁኔታው ያስገነዝባል::

አሁን ባለው ዓለምአቀፋዊ፣ አህጉራዊና አገራዊ ነባራዊ ሁኔታ የነዳጅ ዋጋ ያሻቅብ እንደሆን እንጂ ይቀንሳል የሚል ግምት የለም:: ነዳጅ ደግሞ ከዕለት እንቅስቃሴ ጀምሮ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ላይ ትልቅ ሚና ያለው በመሆኑ እጅግ ይፈለጋል::

በአሁኑ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ኢኮኖሚያዋ ላይ ጫና እየተፈጠረባት ላለው ኢትዮጵያ ደግሞ የነዳጅ ዋጋ መጨመር ነገሮችን አዳጋች ሊያደርጋቸው ይችላል:: በመሆኑም ኢትዮጵያ ምድር የሰጠቻትን ሀብት ወደ ጥቅም መለወጥ ላይ መሥራት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም::

የኢኮኖሚ አቅሟን ማዕከል አድርገው ሊያጠቋት የሚነሱ ኃይሎችን ማሸነፍ የሚቻለው ያለውን ሀብት በአግባቡ አልምቶ መጠቀም ሲቻል ነው:: የውጭ ተጽዕኖ ለርስበርስ ግጭትና ሙስና መስፋፋት መንስኤ ስለመሆኑም አሁን ካለው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ መገንዘብ አያዳግትም:: መንግሥትም ይህንን ታሳቢ በማድረግ በማዕድን ዘርፉ በተለይም በተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ማልማት በኩል ወደ ውጤት የተቃረበ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል::

ከእንቅስቃሴ ተግባራቱ አንዱ በማዕድን ዘርፉ ላይ የነበሩ ክፍተቶችን እየተጠናቀቀ ባለው 2014 አመት የመሙላት እርምጃዎችና እስከ ቅርብ ጊዜ በተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ፍለጋ ጥናት ላይ የተሰማሩ የውጭ ኩባንያዎች ይዘውት የመጡት የጥናት ውጤት ለ20015 ዓ.ም አዲስ አመት መልካም የምሥራችና ተስፋን የሰነቀ ሆኗል::

በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ዘይት አሳሽና አልሚ ኩባንያዎች ከዚህ ቀደም አድርገናል ያሏቸው ጥናቶች ማዕድናቱ በምን ያህል መጠን እንዳሉና ለማልማት ያላቸውን አዋጭነት ያላመላከቱ ነበሩ:: በጥናትና በማልማት ስም የገቡ ኩባንያዎች ለአመታት ለውጤት ያለመብቃታቸውን ጉዳይ በመለየት መንግሥት ፈቃድ እስከመሰረዝ የደረሰ እርምጃ እንዲወስድ ተገዷል::

የማዕድን ሚኒስትሩ ኢንጂነር ታከለ ኡማ የሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸውን የ2014 በጀት አመት የዘጠኝ ወር አፈፃፀም ለሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤በተለያየ የማዕድን ዓይነቶች ኢንቨስትመንት ላይ ተሰማርተው ውጤት ያላስገኙ ፈቃድ የተሰረዘባቸውና በማስጠንቀቂያ የታለፉ መኖራቸውን ማስታወቃቸውን ከዚሁ አኳያ መመልከት ይቻላል::

ከነዚህ ውስጥም ፖሊ ጂሲኤል የተባለው ኩባንያ ይጠቀሳል:: ኩባንያው አራት የፍለጋ አንድ ደግሞ የልማትና ምርት ፍቃድ አግኝቶ ለዘጠኝ አመታት ሲቆይ የሚጠበቅበትን እንዳላከናወነ ለምክርቤቱ ገልጸዋል:: ኩባንያው ባለመስራቱ መንግሥትና ሕዝብ ከፍተኛ ተስፋ የጣለበትን የተፈጥሮ ጋዝ ልማት በተያዘለት ጊዜ እውን እንዳይሆን እንቅፋት መፍጠሩን ተናግረዋል:: ኩባንያው ያለበትን የፋይናንስና የቴክኒክ አቅም ውስንነት እስከ በጀት አመቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ካላሟላ ስምምነቱ የሚቋረጥ መሆኑን ሚኒስቴሩ በደብዳቤ ማሳወቁንም ለምክርቤቱ አሳውቀዋል::

ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ በቅርቡ ደግሞ ሌላ ምስራች ይዞ መጥቷል:: ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ይፋ የተደረገው የምስራች አገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ ነዳጅ ክምችት በሚገባ ያመለካተ ነው::

ከአራት ወር በፊት ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ የአሜሪካ ኩባንያ የሆነው ኤልሲኤአይ (LCAI) በኦጋዴን አካባቢ የነዳጅና የተፈጥሮ ሀብት አቅም አዋጭነት ጥናት የውል ስምምነት ተፈራርሞ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል:: ኩባንያውም በውሉ መሠረት ሥራውን አጠናቅቆ ለሚኒስቴሩ አስረክቧል::

ማዕድን ሚኒስቴር አዲስ ባስጠናው በዚህ ጥናት በኦጋዴን አካባቢ 7 ትሪሊዮን ኪዩቢክ ጫማ ጥልቀት ያለው የተፈጥሮ ጋዝ መኖሩ ተረጋግጧል:: የአሜሪካ ኩባንያ የሆነው ኤልሲኤአይ (LCAI) የጥናትና ውጤቱን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ርክክብ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ በተገኙበት ለሚኒስቴሩ ማስረከቡን ከሚኒስቴሩ የፌስቡክ ገጽ የተገኘው መረጃም ያመለክታል:: መረጃውን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃንም ይዘውት ወጥተዋል::

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በርክክቡ ወቅት «እስከ ዛሬ አለ እየተባለ በአባቶቻችን ሲነገረን የቆየውን የተፈጥሮ ጋዝ ሀብታችን የወደፊት ዕጣ ፈንታችንን የሚወስን አንዱ የአገራችን የኢኮኖሚ ዋልታ እንዲሆን እንሠራለን» ብለዋል። የተፈጥሮ ጋዝ ለአገር ምርት እና ለውጭ ንግድ የምንጠቀምበት ይሆናል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ሰርተፍኬቱ ምን ያክል የተፈጥሮ ጋዝ እንዳለን ያወቅንበት ነው ሲሉም ተናግረዋል። «የሰርተፊኬቱ ሚና አገራችን ያላትን የተፈጥሮ ሀብት፣ እውቀት ልምድና ፍላጎት ሳይኖራቸው አንቀው ከቆዩት በመላቀቅ ሊሠሩና ሊያለሙ የሚችሉ ትላልቅ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ያስችላል» በማለት የማረጋገጫ ሰነዱ የተፈጥሮ ጋዝ እና ድፍድፍ ነዳጅ የማልማት አገራዊ እቅድን አንድ እርምጃ እንደሚያራምድ ጠቅሰው፣ በትልቁ የመንግሥት ቁርጠኝነት የታየበት ሥራ እንደሆነም አመልክተዋል:: እንደሚኒስትሩ ገለጻ ይህ የሰርተፊኬት ሰነዱ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ጋዝ መጠንና የኢኮኖሚ አዋጭነት ማረጋገጫ ነው:: ይህን ሰርተፊኬት በመያዝ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቴክኖሎጂ፣ የፋይናንስ እና በዘርፉ የኢንቨስትመንት አቅም ያላቸው ኩባንያዎች መጋበዝ ይቻላል:: የተዛባ መረጃ ይዘው ሀብታችንን እስረኛ እያደረጉ ላሉ ኩባንያዎችም ጥሩ የማንቂያ ይሆናል ብዬ አምናለሁ ብለዋል ሚኒስትሩ:: ሰነዱን ወደ ተግባር ለመቀየርም ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንና ወደተግባር የመቀየሩ ጉዳይም እንደአሠራራችን ፍጥነት የሚወሰን ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል::

የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ከማጥናት አንስቶ ከምድር በታች ያለውን ሀብት ቆፍሮ ማውጣት፣ ግዙፍ የጋዝ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችን መዘርጋት ከፍተኛ ቴክኖሎጂ፣ ባለሙያና መዋዕለነዋይ የሚጠይቅ ነው:: ይህን ሂደት አልፎ ምርቱን ከፈገር ውስጥ ተጠቃሚነት ባሻገር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ረጅም ጉዞን የሚጠይቅ መሆኑ የማይደርስበት ሊመስል ይችል ይሆናል:: ግን ደግሞ «ህልም አለ ተብሎ ሳይተኛ አይታደርም» እንደሚባለው ሀብት ላይ ቁጭ ብሎ የሚያጋጥሙ ስጋቶችን በማሰብ ወደ ማልማት አለመግባት ሁሌም ከድህነት የማይላቀቅ ሕዝብን ይዞ መጓዝና ከሌሎች ጥገኝነትም የማትላቀቅ ጠባቂ አገር መምራት ይሆናል::

ከዚህ አኳያ መንግሥት አሁን የደረሰበት የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ መጠንን እና የማልማት አዋጭነትን በዘርፉ በሚታወቅ ኩባንያ ማስጠናቱ የአገሪቱን የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ለማልማት ትልቅ ተስፋ ተደርጎ ይወሰዳል፤ በቀጣይም ወደ ልማቱ በመግባት የአገሪቱንና የሕዝቧን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትኩረት መሥራት ይገባል እንላለን::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## መልኬ ውስጥ የበቀሉ ሳቅና እዬዬዎች

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ከእናቴ ጋር ነው የምተኛው..የምነቃውም አብሬዐት ነው። እሷ ጓዳ ጎድጓዳውን ስትንጎዳጎድ ቀሚሷን ይዤ በሄደችበት ሁሉ እከተላታለው። በልጅነቴ የእናቴ ጭራ ነበርኩ። ከጎኗ፣ ከስሯ፣ ከጉያዋ፣ ከቀሚሷ ስር ማንም ፈልጎ የማያጣኝ። ስንተኛ እጇን አናቴ ላይ ጥላ ሳትዳብሰኝና ሳታሻሽኝ ቀርታ አታውቅም። ጭንቅላቴን ሙሉ በእጇ እየዞረች በጎረበጣት ቦታ ላይ ቅማል ያገኘች እየመሰላት በሌባ ጣቷ አናቴን እየቆፈረች በአውራ ጣቷ እገዛ የጎረበጣትን ነገር ከአናቴ ውስጥ መዛ ታወጣለች። አንዳንዴ ቅማል ይቀናታል አንዳንዴ ደግሞ ፎረፎር እጣፈንታዋ ይሆናል። እናቴ በጎረበጣት ቁጥር ቅማል ያገኘች እየመሰላት ብዙ ቀን የደረቀ የአናቴን ፎረፎርና እንዴት እንደገባ ያላስተዋልኩትን ብናኝ እድፍ ተጋፍጣ ታውቃለች።

ዳብሳኝ ዳብሳኝ ሁለት ነገሮች ከአፏ አይቀሩም.. አንድ..እንዳው ከየት አመጣህው ይሄን ከርዳዳ ጸጉር? ድሮ እንዴት ያለ ሉጫ መሰለህ? ስትል ትጠይቀኛለች። ይሄን ወሬዋን ለዘመናት ሰምቼዋለው። እናቴ ጸጉሬን በዳበሰችኝ ቁጥር፣ አናቴ ላይ ቅማል ፈልጋ ባጣች ማግስት ከንፈሯ ላይ የሚጸነስ ወሬ ነው። አልመልሰላትም..እሷም አታብራራልኝም። ‹እንዳው ከየት አመጣህው ይሄን ከርዳዳ ጸጉር? ድሮ እንዴት ያለ ሉጫ መሰለህ› ብላኝ ዝም። ለምን እንደምትጠይቀኝ አላውቅም..ግን ትጠይቀኛለች.. እጇ አናቴ ላይ ሲያርፍ፣ እንደ ሽቦ የጠነከረ ጸጉሬ መዳፏን ሲፈትነው አፏ ነፍስ ይዘራል።

ሁለተኛው ከእናቴ አፍ ላይ የማይጠፋው ቃል ‹ጸጉርህ አድጓል..ያከሳህ እሱ ነው› የሚለው ቃል ነው። ጸጉሬን እየዳበሰችኝ ሰንብታ፣ ቅማል ፍለጋ ባዝና ባዝና አልሆን ባላት ሰሞን ‹ጸጉርህ አድጓል..ያከሳህ እሱ ነው› ትለኛለች። እንዲህ ሳትለኝ ቀርታ አታውቅም። መክሳቴን የማውቀው ያኔ ነው። አንድም ቀን ክሳቴን በመስተዋት አይቼው ወይም ደግሞ ከሌላ ሰው ሰምቼው አላውቅም።

**ከተላጨሁ በኋላ የእናቴ ተቀዳሚ ስራ ጸጉሮቼን ከሜዳ ላይ መሰብሰብ ነው። ‹ጸጉርና ጥፍር የትም አይጣልም› ብላ ጸጉሮቼን ሰብስባ አንድ ጥግ ላይ ትወሽቃቸዋለች**

እንዲህ ባለችኝ በነጋታው ራሴን እናቴ ጉያ ስር አጎንብሼ አገኘዋለው። በግራ መዳፏ ወደ መሬት ደፍታኝ ምላጭ በያዘ ቀኝ እጇ አናቴን እየላጨች። ለግማሽ ሰዐት ያክል በእናቴ መዳፎች ተጽዕኖ ደርሶብኝ እግሯ ስር ተደፍጥጬ ራሴን አገኘዋለው። ጫናዋ ሲበረታብኝ ራሴን ለማዝናናት በተደፈቁበት ላመል እላወሳለው።

‹ምን ያቁነጠንጥሀል? ይልቅ እንዳልቆርጥህ አርፈህ ተቀመጥ› ትለኛለች። በሚያስፈራራና በሚያስጠነቅቅ ድምጽ።

አርፌ መቀመጥ ሳልችል አርፌ ለመቀመጥ እሞክራለው። ግን አይሆንልኝም የእናቴ ድፍጠጣ ሲበረታብኝ ወዲያው ራሴን ካዘነበለበት ቀና ለማድረግ እሞክራለው።

‹አትሰማም እንዴ! እንዳታስቆርጠኝ አትንቀሳቀስ አልኩህ እኮ!› ስትል ትቆጣኛለች። በልጅነቱ መላጨት ስቃይ የሆነበት የመጀመሪያው ሰው እኔ ሳልሆን አልቀርም እላለው። መላጣነቴ ምኑ እንደሚያስደስታት አላውቅም ገና ጸጉሬ ባቆጠቆጠ በሰልስቱ ነበር እናቴ ጸጉሬን መላጨት እንዳለብኝ የምታረዳኝ። ደሞ ውጣ ውረዱ..ዝም ብላ ጉያዋ አድርጋ የምትላጨኝ መሰላችሁ? አይደለም። መጀመሪያ አረፋ ባለው ሳሙና ጸጉሬን ታጥበኛለች። አጥባ አትተወኝም..ድጋሚ ሳሙና ትመታኝና ሳሙናውን ጸጉሬ ላይ እንዳለ ወደ ጉያዋ ታስጠጋኛለች። የሳሙናው መኖር ለምን እንዳስፈለገ ቆይቼ ነው የገባኝ። አንድ ቀን ሳሙናው እያለ አልላጭም ብዬ ሳምጽባት ሳሙናው እኮ ጥሩ ነው.. እንዳትቆረጥ፣ ጥሩ ሆኖ እንድትላጭ ያደርግሀል አለችኝ። ያኔ ነበር ብልሀቷ የተገለጠልኝ። ተላጭቶ ለሚወድቅ ጸጉር ያ ሁሉ እንክብካቤና ሽር ጉድ ይገርመኝ ነበር።

አረፋው አይኔ ውስጥ እየተማገደ ስቃይ ፈጠረብኝ። ለነገሩ ለምጄዋለው..ስላጭ ከነአረፋዬ ስለሆነ አይኖቼ በሳሙናው መለብለባቸው ግድ ነበር። የሳሙናውን ቁጥቋጤ ሰበብ አድርጌ እናቴ ላይ እንደፈለኩ አርጎመጉማለው..እቁነጠነጣለው..ለማልቀስ ይቃጣኛል።

በዚህ መሀል ‹ጨርሻለው..ትንሽ ብቻ ነው የቀረኝ› የሚል የእናቴን ድምጽ እሰማዋለው።

በቃሏ ላይ ተስፋን ጥዬ እረጋጋለው። ወዲያው በሳሙናው፣ በድፈቃው ባጎነበስኩበት እንደ ስንኩል ወዲያ ወዲህ እንፏቀቃለው..

‹አይዞህ..ጨርሻለው በቃ! ስትል ልታባብለኝ ትሞክራለች።

ለለቅሶ የቀረበ ሲቃ የሚመስል ድምጽ እያወጣሁ ባጎነበስኩበት ዝም እላለው..

‹ቁንጮ ላድርግልህ ወይስ ጋሜ? ስትል ትጠይቀኛለች።

አኩርፌ ዝም እላለው..

‹አትናገርም እንዴ?

ማኩረፌን የሚነግራት ዝምታዬ ነው። ዝምታዬ የእናቴን ልብ የሚያራራልኝ ሞገሴ ነው። እናቴ ስትላጨኝ ሳላኮርፍ ቀርቼ አላውቅም። እያኮረፍኩም ቢሆን ላጭታ ትጨርሰኛለች። ቁንጮም ጋሜም ሳታደርገኝ ራሴን ርቃኑን ታስቀረዋለች። አንዳንዴ በእኔ ይሁንታ ቁንጮ አድርጋልኝ ታውቃለች። ጋሜ ምን እንደሆነ አላውቅም። ግን በላጨችኝ ቁጥር ‹ቁንጮ ላድርግልህ ጋሜ? ብላ ትጠይቀኛለች። የቱን መምረጥ እንዳለብኝ ለአፍታ ዝም እላለው። የማላውቀውን ጋሜ መርጬ እዝራ እንዳያበሽቀኝ ስል ብቻ ቁንጮ አድርጊልኝ እላታለው።

ከተላጨሁ በኋላ የእናቴ ተቀዳሚ ስራ ጸጉሮቼን ከሜዳ ላይ መሰብሰብ ነው። ‹ጸጉርና ጥፍር የትም አይጣልም› ብላ ጸጉሮቼን ሰብስባ አንድ ጥግ ላይ ትወሽቃቸዋለች። ቀጥላ ወደ ጓዳ ነው የምትገባው..እሳት በገል ጭራ ተመጣና ከለቃቀመችው ጸጉሬ ጥቂት ታስቀርና እሳቱ ላይ ትጨምራቸዋለች። ከዛም ‹ምቺ እንዳይመታህ ታጠን› ስትል አንገቴን ይዛ ወደ ጭሱ ትደፍቀኛለች።

ከተላጨሁ በኋላም ከመከራ አላርፍም። እናቴ እጇን አናቴ መሀል እያርመሰመሰች ‹ጸጉርህ አድጓል.. ያከሳህ እሱ ነው ካለችኝ ሰዐት ጀምሮ ባለመከራ ነኝ። በመዳፏ ተደፍቄ፣ በአረፋ እየተለበለብኩ ተላጭቼ እንደጨረስኩ ከሁሉም የሚከፋ መከራ ይጠብቀኛል። ወደ ቤት ታስገባኝና ከቅባት እቃው ውስጥ መጠነኛ ቅባት በሌባ ጣቷ ዝቃ መዳፏ ላይ እያሳረፈች በሁለት እጆቿ ታርመጠምጠዋለች። ከዛ መላጣ ራሴን ትቀባዋለች። አቤት ያኔ የምሆነው መሆን..ገና ቅባት ልትቀባኝ እንደሆነ ሳስብ ነበር ልቤ የሚርደው። እናቴ ሳትቆርጠኝ ላጭታኝ አታውቅም። ቅባቱን መላጣዬ ላይ ስትለቀልቀው በጣም ያቃጥለኛል። ያኔ ነፍሴ ከልቤ ውስጥ መሹለክ ያቃጣታል። ያኔ ምን ያክል እንደገበጠችኝ አውቃለው።

ከመላጣነቴ በኋላ እናቴ ጸጉር ያለኝ እየመሰላት እጇን ወደ አናቴ ስትሰድ ከመላጣ አናቴ ጋር ትገናኛለች። በእናቴ መሳሳት በውስጤ እስቃለው። እሷም ጣቶቿን ለመላጣ ራሴ ሳትነፍግ ወዲያ ወዲህ ታርመሰመሳቸዋለች።

ከእናቴ ጋር ያለኝ ቁርኝት ሞቼም የሚከተለኝ ይመስለኛል። በወዲያኛውም አለም ከእናቴ ነፍስ ጋር ዳግም የምጫወት ይመስለኛል። የትም ይሁን መቼም እናቴ አጠገቤ ካለች እጇ ጭንቅላቴ ላይ ነው። ሲዳብሰኝ.. ሲያሻሽኝ የማገኘው ደስታ ዛሬም ውስጤ ይላወሳል። ነፍሴ በዚህ ሁሉ የዘመን እንደናቴ መዳፍ ደስታ ጎብኟት አያውቅም። ከነፍሷ ያጋራችኝ ዛሬም ድረስ የሚከተለኝ ስውር ዳና አለ።

# ዓለም አቀፍ

## ቡርኪናፋሶ ውስጥ ታግተው የነበሩት አሜሪካዊት መነኩሴ ተለቀቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ባለፈው የሚያዝያ ወር ውስጥ ቡርኪናፋሶ በታጣቂዎች ታግተው የነበሩት አሜሪካዊት መነኩሴ ተለቀቁ ሲል የሰሜን ምስራቅ ካያ ሀገረ ስብከት ገለጸ።

የሰሜን ምስራቅ ካያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቴዎፍሎስ ናሬ እንደገለጹት፣ ባሳለፍነው የሚያዝያ ወር ቡርኪናፋሶ ውስጥ በታጣቂዎች ታግተው የነበሩት አንድ አሜሪካዊት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መነኩሴ ተለቀዋል።

ጳጳሱ ቴዎፍሎስ ናሬ በሰጡት መግለጫ "እህት ሱሌይን ቴንሰን በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ጤንነት ላይ ናቸው። ከስጋት ነጻና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ላይ ይገኛሉ" ሲሉ ተናግረዋል።

የ83 ዓመቷ ሱሌይን ቴንሰን የሚጠቀሙበትን መነፅር ብሎም ለደም ግፊት የሚወስዱትን መድሀኒት ሳይዙ እኩለ ሌሊት ላይ ነበር በአካባቢው ከሚኝ ደብር ታግተው የተወሰዱት።

አጋቾቹ ታጣቂዎች ከመሆናቸው ባሻገር አህት ሱሌይን ቴንሰን አግተው ከወሰዱበት የሚያዝያ ወር ጀምሮ እስካሁን ድረስ አጋቾች ማንነታቸው አልታወቀም። ነገር ግን በቡርኪናፋሶ በርካታ ታጣቂ ቡድኖች የሚንቀሳቀሱ




ሲሆን ጥቃትም ይፈጽማሉ።

ጳጳስ ናሬ መነኩሴዋ ሱሌይን ቴንሰን እንዲለቀቁ ያስቻለው ሁኔታ ምን እንደሆነ ምንም አይነት መረጃ የለኝም ብለዋል።

ኤፍቢአይ ከእገታው በኋላ የመነኩሴዋን መጥፋት የሚገልጽ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ አውጥቶ እንደነበርም ጳጳሱ አውስተዋል።

ከአልቃይዳ እና አይ ኤስ ቡድኖች ጋር የሚተባበሩ በርካታ ታጣቂ ቡድኖች በቀጠናው የሚንቀሳቀሱ እንደሆነ የጠቀሱት ጳጳሱ፣ በቡርኪናፋሶ እና በአጎራባች ሀገራት በሰላማዊ ሰዎች ላይ በተደጋጋሚ ጥቃቶች እና አፈናም ሲፈጽሙ ይስተዋላል ነው ያሉት።

የአካባቢው መንግስታት በታጣቂ ቡድኖቹ ላይ ተደጋጋሚ የማጥቃት ዘመቻዎችን ማካሄዳቸውን እንደቀጠሉም ጳጳሱ አመላከተዋል።

**ምንጭ፡- ቢቢሲ**

## ሩሲያ ወደ አውሮፓ ጋዝ የሚያስተላልፈውን ዋና መስመር እንደገና ዘጋች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሩሲያ ወደ አውሮፓ ጋዝ የሚያስተላልፈውን ዋና መስመር እንደገና መዘጋቷን ገለጸች።

ሩሲያ ለጥገና በሚል ወደ አውሮፓ የሚሄደውን ኖርድ ስትሪም 1 የተሰኘውን የጋዝ ማስተላለፊያ ቧንቧዋን እንደገና ዘጋች። በዚህም ለአውሮፓ ከሩሲያ የሚደርሰው የጋዝ አቅርቦት ሙሉ በሙሉ ቆሟል።

በሩሲያ መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደረው ግዙፉ የኃይል ማመንጫ ጋዝፕሮም ኖርድ ስትሪም 1 የነዳጅ ማስተላለፊያ ላይ የተጣለው ገደብ ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናትም ይቆያል ተብሏል።

ሩሲያ ቀደም ሲልም በቧንቧው በኩል ወደ ውጪ የሚላከውን ጋዝ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሳ እንደነበርም ይታወሳል።

ሩሲያ በምዕራባውያን አገራት ዘንድ የኃይል አቅርቦትን እንደ መሳሪያ ተጠቅማለች የሚለውን ክስም ውድቅ አድርጋለች።

የኖርድ ስትሪም 1 የነዳጅ ማስተላለፊያ ቧንቧ ከሩሲያ ባሕር ዳርቻ ሴንት ፒተርስበርግ ተነስቶ በባልቲክ ባሕር ስር አንድ ሺህ 200 ኪሎ ሜትር ሸፍኖ እስከ ሰሜን ምሥራቅ ጀርመን ድረስ የሚዘልቅ የነዳጅ ማስተላለፊያ ቧንቧ ነው ።

ሩሲያ ባሳላፈነው ሀምሌ 21 ላይ ዘግታው የነበረውን የአውሮፓ የነዳጅ ማስተላለፊያ ባንቧን ከፍታው አንደነበር የሚታወስ ነው።

የአውሮፓ ኅብረት በዩክሬን ጦርነት ምክንያት ለጣለው ማዕቀብ ምላሽ ለመስጠት ሩሲያ የጋዝ ቧምቧዋን ባሳላፈነው ሀምሌ 21 ላይ ሙሉ በሙሉ በመዝጋት አቅርቦቷን ታቋርጣለች የሚል ፍራቻ ሰፍኖ አንደነበር ይታወቃል።

በያዝነው ሳምንት ረቡዕ ዕለት ሩሲያ የጋዝ አቅርቦቷን የምታቋርጥ ከሆነ በሚል በሚቀጥሉት ሰባት ወራት አገራቱ የጋዝ አጠቃቀማቸውን 15 በመቶ እንዲቀንሱ የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን አሳስቦም ነበር።

በሩሲያ ነዳጅ ከፍተኛ ጥገኛ የሆነችው ጀርመንም ሆነ ሌሎች የአውሮፓ አገራት ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን የሚያስፈልጋቸውን ነዳጅ ያቀርባሉ የሚል አመኔታ አጥተዋል።

በሙቀትና ማዕበል በተመታችው አውሮፓ ያሉ አገራት ሚኒስትሮች አገሪቱ ለመጪው ቅዝቃዜ ወቅት በቂ የተከማቸ ጋዝ እንደሌላቸው ተረድተውታል።

አውሮፓውያን ዜጎቻቸው የኃይል አጠቃቀማቸውን እንዲቀንሱ እየተማጸኑ ነው። በተጨማሪም ከሌሎች አገራት ፈሳሽ የተፈጥሮ ጋዝ አቅርቦትን ለማግኘት እንዲሁም በበርካታ አገራት እንዲቀር የተደረገውን ከድንጋይ ከሰል ኃይል ለማመንጨትም እየሞከሩ ነው።

በአውሮፓውያኑ 2011 አገልግሎት መስጠት የጀመረው የነዳጅ ማስተላለፊያ ቧንቧው በቀን ከፍተኛውን 170 ሚሊዮን ኪዩቡክ ሜትር ጋዝ ከሩሲያ ወደ ጀርመንም መላክ የሚችል እንደነበረም ተነግሯል።

ከዚህ ቀደም ሩሲያ በየዓመቱ ለምታካሂደው የጥገና ሥራ ለአስር ቀናት ዘግታው የነበረ ሲሆን፣ ከተከፈተ በኋላም ማስተላለፍ ከሚችለው አቀም በታች 20 በመቶ አቅም ብቻ እየሰራ የነበረ ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ ሩሲያ ለነዳጅ ስርጭቱ ችግር ያለባቸው መሳሪያዎች ስላሉ ነው ብላለች።

የጀርመን የኔትወርክ ተቆጣጣሪ ፕሬዝዳንት ክላውስ ሙለር ፣ ሩሲያ በሚቀጥሉት ቀናት አቅርቦት ከጀመረች አገሪቱ ባላት ክምችት መቋቋም እንደምትችል ተናግረዋል።

ክላውስ ሙለር በንግግራቸው "ችግሩን ለመቋቋም እንደምንችል እገምታለሁ፤ ሩሲያ በመጪው ቅዳሜ 20




በመቶ መላክ እንደምትጀምር አምናለሁ፤ ነገር ግን ማንም በትክክል ይህንን በእርግጠኛነት መናገር አይችልም" በማለት ተናግረዋል።

ነገር ግን የጀርመኑ ኢኮኖሚ ሚኒስትር ሮበርት ሃቤክ እንደተናገሩት፣ የሩሲያ እርምጃ ከወዲሁ አንዳንድ የጀርመን ኩባንያዎች ምርታቸውን እንዲያቆሙ አስገድዷቸዋል። በአሁኑ ወቅት የተፈጠረው ጉዳይ "አሳዛኝ ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

የዜና ምንጭ፡- ሮይተርስና ፋይናንሺያል ታይምስ

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ዓርብ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት
ነው!

# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በብራሰልስ ዳይመንድሊግ ስድል ይጠበቃሉ

ብርሃን ፈይሳ

ከኳታሯ ዶሃ የጀመረው ዓመታዊው የዳይመንድ ሊግ ውድድር 85 የሚሆኑ የኦሊምፒክ እና የዓለም ቻምፒዮና የሜዳሊያ አሸናፊዎችን በተለያዩ 13 ከተሞች አፎካክሮ ሊገባደድ ደርሷል። ለአራት ወራት ያህል በበርካታ የአውሮፓ እንዲሁም በአንድ አንድ የሰሜን አሜሪካ፣ እስያ እና አፍሪካ ከተሞች በተለያዩ የአትሌቲክስ ዲሲፕሊኖች ሲደረግ የቆየው ይህ ውድድር ከቀናት በኋላ ይቋጫል። ዛሬ በቤልጂየም ዋና ከተማ ብራሰልስ የሚካሄደውን ውድድር ተከትሎ ከጥቂት ቀናት እረፍት በኋላ በስዊዘርላንድ ዙሪክ የዳይመንድ ሊጉ አጠቃላይ አሸናፊዎች የሚለዩ ይሆናል።

ከመላው ዓለም የተውጣጡትና በተለያዩ ከተሞች ባደረጓቸው ውድድሮች ነጥቦችን ሲሰበስቡ የቆዩት የስፖርቱ ምርጥ አትሌቶች የመጨረሻውንና ወሳኙን ውድድር ዛሬ ያደርጋሉ። ለዚህም የሉዛኑ ሚሞሪያል ቫን ዳም ስታዲየም የመም እና የሜዳ ተግባራት ውድድሮችን ለማስተናገድ ዝግጁ ሆኗል። 14 ዓይነት የአትሌቲክስ ውድድሮች የሚካሄዱ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል በሆኑት የአጭርና መካከለኛ ርቀት ውድድሮች ላይ ተካፋይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለዳይመንድሊጉ አጠቃላይ አሸናፊነት ወደሚያደርጉት ግስጋሴ ይበልጥ እንደሚጠጉ ይጠበቃል።

በሴቶች ዘርፍ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በ3ሺ ሜትር መሰናክል እንዲሁም በ1ሺ500 ሜትር ተካፋይ እንደሚሆኑ ታውቋል። በዓመቱ መልካም የሚባል ብቃት እያሳዩ ያሉት እንዲሁም የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ጨምሮ በተለያዩ ውድድሮች ላይ ስኬታማ የሆኑ አትሌቶች በሚካፈሉበት በዚህ ውድድር ላይ ኢትዮጵያውያኑ እርስ በእርስ የሚኖራቸው ፉክክር እንደሚበረታም ይጠበቃል።


ወርቅውሃ ጌታቸውና መቅደስ አበበ በሞናኮ ያሳዩትን ድንቅ ብቃት ዛሬ በብራሰልስ እንደሚደግሙ ይጠበቃል፣

በ3ሺ መሰናክል በኦሪጎን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ በማጥለቅ በርቀቱ አገሯን ያስጠራችው አትሌት የወርቅውሃ ጌታቸው ተወዳዳሪ ናት። የወርቅውሃ ሞናኮ ላይ ማሸነፏ የሚታወስ ሲሆን፤ በወቅቱ የገባችበት ሰዓትም 9:06.19 ሆኖ ተመዝግቦላታል። የወርቅውሃ በርቀቱ ያላት ፈጣን ሰዓት ደግሞ 8 ደቂቃ ከ54 ሰከንድ ከ61 ማይክሮ ሰከንድ ነው። አትሌቷ ባላት ፈጣን ሰዓት ቀዳሚዋ ስትሆን፤ ከወቅታዊ አቋሟ ጋር ተያይዞም የዛሬውን ውድድር የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖራት ይጠበቃል። ተፎካካሪዎቿም ቢሆኑ የሌላ አገር አትሌቶች ሳይሆኑ የአገሯ ልጆች ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው የሚገመተው።

ሌላኛዋ የውድድሩ ተጠባቂ አትሌት ደግሞ መቅደስ አበበ ናት። በኦሪጎን የወርቅ ውሃን ተከትላ በመግባት ለአገሯ የነሐስ ሜዳሊያ ያስገኘችው አትሌቷ በዶሃው ዳይመንድ ሊግ ተካፋይ ነበረች። አትሌቷ 8 ደቂቃ ከ56 ሰከንድ ከ08 ማይክሮ ሰከንድ የሆነ የግሏ ፈጣን ሰዓት አላት። ዘርፌ ወንድምአገኝም በዛሬው ውድድር የምትሳተፍ ሌላኛዋ ወጣት አትሌት ናት። አትሌቷ በሞናኮው ዳመንድሊግ ላይ የወርቅውሃን ተከትላ መግባት የቻለች ሲሆን፤ በማይክሮ ሰከንዶች ብቻ ተቀድማም 9:06.63 የሆነ ሰዓት አስመዝግባለች። ይህም በርቀቱን ያስመዘገበችው ፈጣኑ ሰዓቷ ነው።

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በስፋት የሚካፈሉበት ሌላኛው ርቀት ደግሞ 1ሺ500 ሜትር ነው። በዚህ ውድድር ላይ የአሸናፊነት ቅድመ ግምት ያገኘችው አትሌት ደግሞ ፍሬወይኒ ኃይሉ ናት። በዚህ ርቀት በቶኪዮ ኦሊምፒክ እንዲሁም በዩጂኑ የዓለም ቻምፒዮና አገሯን የወከለችው ፍሬወይኒ የዲፕሎማ ባለቤት መሆኗ የሚታወስ ነው። በርቀቱ 3፡56፡28 የሆነ ሰዓት ያላት ይህች አትሌት የውድድሩ አሸናፊ ልትሆን እንደምትችል ይጠበቃል።

ለፍሬወይኒ ፈተና እንደምትሆን የምትጠበቀው አትሌት ደግሞ ድርቤ ወልተጂ ናት። ድርቤ በዛሬው ውድድር ከሚሳተፉ አትሌቶች ከፍሬወይኒ በማይክሮ ሰከንዶች የዘገየ ፈጣን ሰዓት ያላት ሆና የተቀመጠች ሲሆን፤ ባለፈው ወር መጀመሪያ በፖላንድ በተካሄደ የዳይመንድሊግ ውድድር በርቀቱ የቦታውን ክብረወሰን በመስበር ጭምር ማሸነፍ የቻለች አትሌት መሆኗ ይታወቃል። ይህም ድሏን በድጋሚ ብራሰልስ ላይ ለማጣጣም እንደምትሮጥ ተጠባቂ አድርጓታል። አክሱማዊት እምባዬ እና አያል ዳኛቸውም በተመሳሳይ ከፍተኛ የአሸናፊነት ፍልሚያ እንደሚያደርጉ ከሚጠበቁት አትሌቶች መካከል ናቸው።

በወንዶች በኩል ዛሬ በብራሰልስ የሚሮጠው ብቸኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዮሚፍ ቀጀልቻ ነው። በ5ሺ ሜትር ርቀት የሚሮጠው አትሌቱ ከሁለት ወር በፊት ሮም ላይ በመሮጥ 12:52.10 የሆነ ሰዓት ነበር ያስመዘገበው። አትሌቱ በርቀቱ 12፡46፡79 የሆነ ሰዓት ያለው ሲሆን፤ በዛሬው ውድድርም ለማሸነፍ እንደሚሮጥ ይጠበቃል።




## በጋዜጦቻችን መፃፍ ይፈልጋሉ?

የድርጅታችን የህትመት ውጤቶች በሆኑት ጋዜጦቻችን ላይ መፃፍ ይፈልጋሉ? በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በእንግሊዘኛ፣ በትግርኛ፣ በሲዳሙአፎ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ነፃ ሀሳብዎን የሚያስተናግዱ አምዶችን አዘጋጅተናልና ያለዎትን ሃሣብ ይላኩልን።

ኢፕድ

0011 1264341
00111264339
ፋክስ 0111569862
Website www.press.et
email epapromotion@press.et

ድርጅታችን በሚያሳትማቸው ዕለታዊ ጋዜጦች አዲስ ዘመን እና ዘኢትዮጵያን ሄራልድ፣ በሳምንታዊዎቹ በሪሳ፣ ባካለቾ፣ ወጋህታ እና አልዓለም እንዲሁም በሁለት ወር አንድ ጊዜ በምትታተመው ዘመን መጽሔት ላይ አገልግሎትዎን እና ምርትዎን ያስተዋውቁ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ